# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 093 ታኅሣሥ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ለዓባይ ግድብ
## የሚሰበሰበው ገቢ በእጥፍ ጨምሯል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለዓባይ ግድብ የሚሰበሰበው ገቢ በእጥፍ ማደጉን የማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ አስታወቀ፡፡

የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሀይሉ አብርሃም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከኅብረተሰቡ ለዓባይ ግድብ የሚሰበሰበው ገቢ በአማካይ ሲታይ እጥፍ የሚጠጋ ዕድገት አሳይቷል፡፡

ከለውጡ በፊት በዓመት ይሰበሰብ የነበረው ገቢ 900 ሚሊዮን ብር ገደማ ነበር ያሉት ዳሬክተሩ፤ ከለውጡ በኋላ በዓመት በአማካይ ከአንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን በላይ ብር ገቢ እየተገኘ ነው ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡

የሚሰበሰበው ገቢ በተለያዩ ምክንያቶች ከዓመት ዓመት የመዋዠቅ አዝማሚያ ቢያሳይም አማካዩ ሲታይ ከፍተኛ ነው ብለው፤ በ2013 ሁለት ነጥብ ሁለት፤ በ2014 አንድ ነጥብ ስድስት እና በ2015 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር መገኘቱን እንደማሳያ ጠቅሰዋል፡፡

የሚሰበሰበው ገቢ ላይ ከዚህ በላይ ለውጥ መመዝገብ ይችል እንደነበር የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ በአንዳንድ ክልሎች በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ አለመረጋጋቶች ገቢው ከዚህ እንዳይበልጥ እንቅፋት መፍጠራቸውን አስረድተዋል፡፡

በአማራ፣ በትግራይ፣ በአፋርና በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ግጭቶችና አለመረጋጋቶች በመኖራቸው

ለዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ4 ዞሯል


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia





# በክልሉ በ3 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሄክታር ላይ የሚገኝ ምርት ተሰብስቧል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል እስከ አሁን በ3 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሄክታር ላይ የሚገኝ ምርት መሰብሰቡን የክልሉ ግብርና ቢሮ ገለጸ።

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ቃልኪዳን ሽፈራው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ እንደ ክልል በመኸር ወቅት 5ነጥብ1 ሚሊዮን ሄክታር በተለያዩ ሰብሎች በዘር ተሸፍኗል፡፡ አሁን ወቅቱ የምርት ማሰባሰብ ሥራ የሚሰራበት

በክልሉ ... ወደ ገጽ4 ዞሯል



ገበየሁ ሲካሳ(ዶ/ር)

## በአዲስ አበባ 70 በመቶ የሚሆነው የኃይል መቆራረጥ የሚያጋጥመው በዛፎች ምክንያት ነው

- አገልግሎቱ በ121 ሠራተኞቹ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ወስዷል

ገጽ 4

# ባንኩ ኢትዮጵያን በግብርና እና ማዕድን ዘርፎች ለማዘመን እየሠራ ነው

## - ከ200 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ማሽነሪዎችን ለደንበኞቹ አስረክቧል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የግብርና እና ማዕድን ዘርፎችን ለማዘመን ሚናውን እየተወጣ መሆኑን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አስታወቀ፡፡ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የማአድንና ግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ ለ39 የሊዝ ፋይናንስ ደንበኖቹ 200 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸውን ማሽነሪዎች በትናንትናው እለት አስረክቧል።

በመድረኩ ላይ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው እንደገለፁት፤ ባንኩ በሀገሪቱ ግብርና እና ማዕድን ዘርፎችን ለማዘመን የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እየተወጣ ነው፡፡ በዚህም የግብርናና ማእድን ዘርፍን ለመደገፍ ጥራት ያላቸውን ማሽኖች በዘርፉ ለተሰማሩ ደንበኞች አስረክቧል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዘመናዊ የእርሻ ማሽኖችን በማቅረብ የግብርና ዘርፉን እየደገፈ መሆኑን

ባንኩ ... ወደ ገጽ4 ዞሯል










# የመነ አቢቹ ነዋሪዎች በማኅበራዊ እና መሰረተ ልማት ችግሮች መማረራቸውን ገለጹ

## - የክፍለ ከተማው አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት እየሠራሁ ነው ብሏል

ሸገር፡- በሸገር ከተማ የመነ አቢቹ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች በማህበራዊ አገልግሎት፣ በኑሮ ውድነት፣ በመሰረተ ልማትና በፀጥታ እየተፈተኑ መሆኑን ገለጹ፡፡ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት እየተሠራ ነው ሲሉ የክፍለ ከተማው አስተዳዳሪ ተናግረዋል፡፡

በሸገር ከተማ የመነ አቢቹ ክፍለ ከተማ ነዋሪ አቶ ካሊድ አብደላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ክፍለ ከተማው በማህበራዊ አገልግሎት፣ በኑሮ ውድነት፣ በመሰረተ ልማትና በፀጥታ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን እየፈታ አይደለም፡፡ ከበርካታ ዓመታት በፊት የነበሩ ችግሮች አሁንም ቀጥለዋል፡፡

በከተማው ያለው መሰረተ ልማት ችግር ተባብሷል ያሉት አቶ ካሊድ፤ የኑሮ ውድነቱም እያደር መባባሱንና ምንም ዓይነት ለውጥ እያዩ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሸገር ከተማ የመነ አቢቹ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ሜሮን ኤርሚያስ በበኩላቸው፤ በክፍለ ከተማው የማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነት የሚታዩ ለውጦች አሉ። ሆኖም የኑሮ ውድነት፣ የመሰረተ ልማት እና የፀጥታ ስጋት ችግሮች አሉ ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሜሮን ገለፃ፤ በክፍለ ከተማው መታወቂያ ለማውጣት ተገቢ አገልግሎት እየተሰጠ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ የጤና ጣቢያ አገልግሎቶች ላይም ችግሮች አሉ፡፡

"ማህበረሰቡ የደህንነት ስጋት አለበት፤ በሰላም ወጥቶ ለመግባት እየተቸገረ ነው" ያሉት ደግሞ የክፍለ ከተማው ነዋሪ ፓስተር ዘላለም መዝገቡ ናቸው፡፡ በክፍለ ከተማው የቤት ኪራይና የኑሮ ውድነት፣ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነት ላይ ችግር አለ ብለዋል፡፡



አቶ አብርሃም ብርሀኑ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የነዋሪውን ጥያቄዎች ይዞ ያነጋገራቸው የሸገር ከተማ የመና አቢቹ ክፍለ ከተማ ዋና አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም ብርሀኑ የተነሱ ቅሬታዎች ትክክል መሆናቸውን አምነዋል፡፡

በማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥና ተደራሽነት፣ በኑሮ ውድነት፣ በመሰረተ ልማትና በፀጥታ ዙሪያ የሚታዩ አንዳንድ ችግሮችን ለመፍታት እየተሰራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ክፍለ ከተማው ከመቋቋሙ በፊት የነበሩ የመሰረተ ልማት፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የፀጥታ ውዝፍ ችግሮችን ለመፍታት በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል ብለዋል፡፡

የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን የመገንባትና ለአገልግሎት ክፍት የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው ያሉት አስተዳዳሪው፤ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የትምህርትና የህክምና ቁሳቁሶችን የማሟላት ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ትምህርት ቤቶችም የማስገንባትና የማደስ ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ገልጸዋል። በክፍለ ከተማው አምስት ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ መድኃኒት ቤት ግንባታ እየተካሄደ መሆኑንም አያይዘው ገልጸዋል፡፡ ሦስት ኪሎ ሜትር የጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ መንገድም ተሠርቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በአንዳንድ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በቂ የሆነ የመስሪያ ግብዓት፣ የሰው ኃይል፣ የእውቀትና የክህሎት ብቃት አለመኖሩ ችግር እንደፈጠረ ጠቅሰው፤ የግል ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚሰሩ አንዳንድ አካላት አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ክፍተቶች እንዳሉ ነው የተናገሩት።

ክፍተቶችን ለማስተካከልና ማህበረሰቡ የሚፈልገውን አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የበላይ አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በክፍለ ከተማው እየገጠመ ያለውን የኑሮ ውድነትን ለማርገብ ምርታማነትን የማሳደግና የሥራ እድል የመፍጠር ሥራ እየተሰራ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በፀጥታ በኩል የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የፀጥታ መዋቅሩ ከማህበረሰቡ ጋር በቅንጅት እየሰራ እንደሚገኝም አመላክተዋል፡፡



# የጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል የማስፋፊያ ግንባታ በአራት ወራት ይጠናቀቃል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ እየተካሄደ የሚገኘው የጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል የማስፋፊያ ግንባታ በሚቀጥሉት አራት ወራት እንደሚጠናቀቅ ሆስፒታሉ ገለጸ፡፡

የጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ ዶክተር እሸቱ ታደለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ለበርካታ ህሙማን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

ሆስፒታሉ በ2014 ዓ.ም በ551 ሚሊዮን ብር ወጪ የማስፋፊያ ግንባታ ለማካሄድ ውል ተገብቶ ሥራ የጀመረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች በተያዘለት ጊዜና ወጪ ግንባታው እስካሁን አልተጠናቀቀም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የማስፋፊያ ግንባታውን በአራት ወራት ለማጠናቀቅ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ዶክተር እሸቱ በአሁኑ ጊዜ የሆስፒታሉ ማስፋፊያ ግንባታ አፈጻጸም 45 በመቶ የደረሰ መሆኑን ገልጸው፤ ህንጻውን በዚህ በጀት ዓመት በማጠናቀቅ ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ሆስፒታሉ ባለ ዘጠኝ ወለል ሲሆን 470 አልጋዎች፣ 9 የቀዶ ጥገና ማዕከላት፣ 67 የጽኑ ህክምና ፣የሲቲስካን ፣ የኤምአራይና ሌሎች አስፈላጊ ክፍሎች የያዘ እንደሚሆን ጠቅሰዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ እንደገለጹት፤ ሆስፒታሉ በከተማዋ የመጀመሪያው የድንገተኛ አደጋ ህክምና መስጫ እንዲሆን ታልሞ እየተሰራ ሲሆን፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለአቃቂ ክፍለ ከተማ ብቻ ሳይሆን እንደ አዲስ አበባም በሌሎች ሆስፒታሎች ላይ ያሉ ጫናዎችን በመቀነስ ብዙ ለውጦች ያመጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል የማስፋፊያ ግንባታ የህንጻ ተቋራጭ ቴክኒካል ማናጀር ናትናኤል ስማቸው በበኩላቸው ሆስፒታሉ 511 ክፍሎች ያሉት መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህ ክፍሎች የድንገተኛ አደጋ ህክምና መስጫ ናቸው ብለዋል፡፡

የሆስፒታሉን የማስፋፊያ ሥራ በተለያዩ ምክንያቶች በተያዘለት ጊዜና ወጪ ማጠናቀቅ አለማቻሉን ሥራ አስኪያጁ አውስተው፤ ግንባታው ይካሄድበታል ተብሎ የተለየው ቦታ መቀየር፣ የካሳ ጉዳዮች መዘግየት ፣ የዲዛይን ለውጥ መደረጉና የግብአት እጥረት ማጋጠሙ ዋና ዋና ምክንያቶች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

ግንባታው ከጊዜ ባለፈ ተጨማሪ ገንዘብን የጠየቀ ሲሆን፤ አጠቃላይ በጀቱ ወደ 656 ሚሊዮን ብር ከፍ እንዲል መደረጉንና እስካሁን በተሰሩ ስራዎችም 39 ነጥብ አምስት በመቶ ገንዘብ መጠቀሙን ገልጸዋል፡፡

አሁን ላይ የሆስፒታሉ የማስፋፊያ ግንባታ አፈጻጸም 45 በመቶ መድረሱን የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ ፕሮጀክቱ ለታለመለት ዓላማ በፍጥነት እንዲደርስ ከተማ አስተዳደሩ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑንና ይህን ድጋፍ እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ግንባታውን በቀጣይ አራት ወራት ውስጥ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡



# ክልሉ ሙስናን የሚጸየፍና የሚታገል ትውልድ ለመፍጠር እየሠራ ነው

## - ከ518 ሚሊዮን ብር በላይ ወደ መንግሥት ካዝና ተመልሷል

**ማርቆስ በላይ**

አዳማ፡- የኦሮሚያ ክልል ሙስና በሀገር ላይ የሚያስከትለውን ችግር ተረድቶ የሚጸየፍና የሚታገል ትውልድ ለመፍጠር እየሰራ መሆኑን የክልሉ ሥነ ምግባር ጸረ ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ። ከ518 ሚሊዮን ብር በላይ ወደ መንግሥት ካዝና ተመላሽ መደረጉም ተገልጿል።

በክልል ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ "ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፤ በኅብረት እንታገል" በሚል መሪ ሀሳብ ዓለም አቀፍ የጸረ ሙስና ቀን ትናንት ተከብሯል።

የኦሮሚያ ክልል ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽነር አብደላ አገቴ በመርሃግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ሙስና በሀገር የሚያስከትለውን ችግር ተረድቶ የሚጸየፍና የሚታገል ትውልድ መፍጠር ያስፈልጋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ በክልል የሙስናን እንቅስቃሴ ለመግታትና የሕግ የበላይነትን ለማስከበር የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደዋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታት ከስድስት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱን ገልጸው 518 ሚሊዮን ብር በላይ እና ከአንድ ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ወደ መንግሥት ካዝና ተመልሷል ብለዋል።

ሙስና ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግርን የሚያመጣ ተግባር ነው ያሉት ኮሚሽነር አብደላ፤ ሙስናን እንደ ሀገር በጋራ በመቆም መታገል ያስፈልጋል ብለዋል።

ሙስና የሚፈጸምበት መንገድ ውስብስብና በተቀናጀ ሁኔታ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስልቱን የሚቀያይር በመሆኑ ሙስናን በጋራ ልንታገለው ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የሙስና መስፋፋት የሕግ የበላይነት እንዳይከበር በማድረግ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጣሱ የሚያደርግ መሆኑን በመግለፅ፤ ሕገ ወጥነትን በማስፋፋት የዜጎችን ደህንነት ስጋት ውስጥ ያስገባል ብለዋል፡፡

ሙስና የጋራ ጠላታችን በመሆኑ በኅብረት መታገል አለብን ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ሙስና የኢኮኖሚያዊ የማህበራዊና የፖለተካዊ ጉዳዮች እንቅፋት በመሆን ትልቅ ችግር እያስከተለ ነው ብለዋል።

በትምህርት ተቋማት ሙስናን መሸከም የማይችል ትውልድ መፍጠር እንደሚገባ ጠቅሰው፤ በተቋማት ደረጃ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መቅረፍ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የክልሉ ጸረ ሙስና ኮሚሽን በሙስና ተግባር የተሳተፉ አካላትን ተጠያቂ ለማድረግ እንደሚሰራ ጠቅሰው፤ ኅብረተሰቡ ሙሰኞችን በማጋለጥ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርግ አሳስበዋል።

የጨፌ ኦሮሚያ ምክትል አፈ ጉባኤ ኤሊያስ ኡመታ በበኩላቸው፤ የዕለቱ መከበር ዋነኛ አላማ ሙስናን መከላከል በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ነው።

የሙስናን አስከፊነት በመረዳት ሙስናን የሚጸየፍና የሚታገል ትውልድ መፍጠር ያስፈልጋል ያሉት ምክትል አፈ ጉባኤው፣ ሙስናን በመጠቀም በአቋራጭ ለመክበር የሚደረግ ተግባርን መታገል እንደሚያስፈልግ ነው የገለጹት።

ሙስናን ለመከላከል እየተወሰዱ ያሉ ተግባራት ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ በመግለፅ መንግሥት ሙስናን ለማስቀረትና ዜጎችን በታማኝነት ለማገልገል የሚሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የጨፌ ኦሮሚያ ምክትል አፈ ጉባኤ ኤሊያስ ኡመታን ጨምሮ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ መስከረም ደበበና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# የክልሉ መንግሥት የኃይል አማራጭን በመተው ወደ ሰላም ለሚመለሱ ኃይሎች የሰላም ጥሪ አስተላለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ባህርዳር፡- የአማራ ክልል መንግሥት የኃይል አማራጭን በመተው ወደ ሰላም ለሚመለሱ ኃይሎች የሰላም ጥሪ አስተላለፈ፡፡

የክልሉ መንግሥት ያወጣውን የሰላም ጥሪ አስመልክቶ የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) በሰጡት መግለጫ፤ አሁን ላይ በክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን መታደግ በመቻሉና፣ የክልሉ ሰላም ሁኔታ በእጅጉ እየተሻሻለ በመምጣቱ ይህንንም ሰላም ዘላቂ ለማድረግ የሰላም ጥሪ ማድረግ አስፈልጓል ብለዋል።

የሰላም ጥሪው ተጨማሪ ደም መፋሰስን ለማስቀረት መንግሥት በሆደ ሰፊነት የከፈተው የሰላም በር ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብን ፀጥታ እና ደህንነት አደጋ ላይ የጣለውን ሕገ-ወጥ የኃይል እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር እና ለመቀልበስ በጀግናው የመከላከያ ሠራዊት፣ በክልሉ የፀጥታ ኃይሎች እና በክልሉ ሕዝብ በተከፈለው ክቡር መስዋዕትነት በክልሉ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን መታደግ በመቻሉ እና በክልሉ ያለው የፀጥታ ሁኔታ በእጅጉ እየተሻሻለ መምጣቱን መግለጫው አትቷል፡፡

የክልሉን ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በማፍረስ ክልሉን ከፌዴራል መንግሥት በመነጠል የትርምስ ቀጠና ማድረግ ግቡ የነበረውን እንቅስቃሴ ለማክሸፍ እና የሕግ የበላይነትን ለማስከበር በሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ በክልሉ የፀጥታ ኃይሎች እና በሕዝብ ርብርብ በተወሰዱ እርምጃዎች በክልሉ የሚታየው የሠላም ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ በእጅጉ እየተሻሻለ የመጣ በመሆኑ እና ይህንን አንፃራዊ ሰላም ይበልጥ ለማጽናት የሰላም ጥሪ ማድረግ ማስፈለጉንም ጠቁመዋል፡፡

በጽንፈኝነት የተቃኘ እና የግል ፍላጎትን ማዕከል ያደረገ አላማ ባነገቡ ጥቂት ግለሰቦች እና ቡድኖች ቅስቀሳ የተሳሳቱ ወጣቶች እና የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከስህተት መንገድ የሚመለሱበትን ሰላማዊ መንገድ ማመቻቸት ስለሚገባ ጥሪው ማስፈለጉንም መግለጫው አትቷል፡፡

በክልሉ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ ከሕዝብ ጋር በተደረጉ ተከታታይ ውይይቶች የሕግ የበላይነትን ባረጋገጠ አግባብ ለታጣቂ አካላት የሰላም ጥሪ ቀርቦ ግጭቱ እንዲያበቃ እና አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ከሕዝብ የተነሳውን ጥያቄ በመቀበል አስፈላጊ መሆኑንም አብራርቷል፡፡

ተጨማሪ ደም መፋሰስን፣ጥፋትን እና ውድመትን ለማስቀረት መንግሥት በሆደ-ሰፊነት የሰላም አማራጮችን አሟጦ የመጠቀም ጥረቱን ማስቀጠል ለሀገር እና ለሕዝብ ያለውን ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት እና የፖለቲካ አጀንዳ እና ጥያቄዎች በሰላማዊ እና ሕጋዊ መንገድ ብቻ ዘላቂ መፍትሄ እንደሚያገኙ በፅኑ በማመን እና ለሰላማዊ የፖለቲካ ውይይት እና ምክክር መንገድ የሚጠርግ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን በማመን መግለጫው መውጣቱንም አብራርቷል፡፡

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጠቅላይ መመሪያ ዕዝ ጋር በመመካከር ስምምነት በተደረሰበት አቅጣጫ እና የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 6 /2015 አንቀጽ 5(4) (ሠ) እና 6(12) መሰረት በማድረግ ይህ የሰላም ጥሪ የውሳኔ ሃሳብ ተላልፏል ብሏል።

በዚህም መሰረት የውሳኔ ነጥቦች፣ ይህ ጥሪ ለሕዝብ ይፋ ከተደረገ ጀምሮ በሚቆጠር ሰባት ቀናት ውስጥ በየትኛውም ኢ-መደበኛ አደረጃጀት እና ትጥቅ ትግል ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ታጣቂዎች ባሉበት አካባቢ በሚገኙ የኮማንድ ፖስት አዛዦች ለዚሁ አላማ ለይተው ለሕዝብ ወደሚያሳውቋቸው የመሰብሰቢያ ስፍራዎች በመሄድ ወደ ሰላማዊ ህይወት ለመመለስ ያላቸውን ፍላጎት እንዲያሳውቁ ጥሪ ቀርቧል።

ከዚህም በተጨማሪ በየአካባቢው ያሉ የቀጣና ኮማንድ ፖስት አመራሮች፣ የአካባቢው አስተዳደር እና



**መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር)**

የፖለቲካ አመራሮች እንዲሁም የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍል ተወካዮች እና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመተባበር ወደ ሰላማዊ ህይወት ለመመለስ ፍላጎት ኖሮዋቸው ወደ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ከላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የሚመጡትን ሁሉ በአግባቡ በመቀበል፣ የህክምና አገልግሎት እና መሰል አጣዳፊ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸውም አስፈላጊውን ትብብር በማድረግ እንዲያስተናግዱ እና ወደተሃድሶ ማዕከላት እንዲወስዱ መመሪያ ተሰጥቷል።

በሦስተኛ ደረጃም የቀጣና ኮማንድ ፖስት አመራሮች እና ተሃድሶ ማዕከላት አስተባባሪዎች ወደ ሰላማዊ ኑሮ የሚመለሱ የቀድሞ ታጣቂዎች በተሃድሶ ማዕከላት ውስጥ አስፈላጊውን የተሃድሶ ስልጠና እንዲያገኙ፣ ወደ ማኅበረሰቡ ተቀላቅለው በሰላም ለመኖር የሚያስችላቸውን የአዕምሮ ዝግጅት ለማድረግ አስፈላጊው የሥነ-ልቦና፣ ምክር እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማድረግ የተሃድሶ መርሀ ግብር መጨረሳቸውን እያረጋገጡ የምስክር ወረቀት እንዲሰጡ መመሪያ ወርዷል።

ለሕግ እና ፍትሕ አካላት የተሃድሶ መርሀ ግብር ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ያገኙ የቀድሞ ታጣቂዎች በግጭቱ አውድ ውስጥ የተፈፀሙ በምህረት ሊሸፈኑ የሚችሉ ወንጀሎችን በተመለከተ የምህረት ተጠቃሚ እንደሆኑ በመገንዘብ እነዚህ ግለሰቦች ላይ ከነዚህ ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የተጀመሩ የምርመራ፣ የክስም ሆነ የፍርድ ማስፈፀም ሂደቶችን በማቋረጥ ተገቢውን ትብብር እንዲያደርጉ መመሪያ መተላለፉን አውስቷል።

የክልል፣ ዞን፣ ወረዳ እና ቀበሌ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር አካላት እና አመራሮች ይህን የሰላም ጥሪ ተቀብለው ለሚመለሱ የቀድሞ ታጣቂዎች ወደ ሰላማዊ ኑሮ መመለስ እንዲችሉ ተገቢውን ትብብር እንዲያደርጉ፣ በተለይም እነዚህ ዜጎች በሰላማዊ እና ሕጋዊ አግባብ የፖለቲካ ግብ እና አጀንዳቸውን ማራመድ ይችሉ ዘንድ ምቹ አውድ እና የውይይት መድረኮችን እንዲያመቻቹ መመሪያ መሰጠቱን አስታውቋል።

ይህንን የሰላም ጥሪ በየደረጃው ካሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እዞች ወይም ኮማንድ ፖስቶች ጋር በመቀናጀት እንዲያስፈፅም እና ለአፈፃፀሙ አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መመሪያዎችን እንዲያወጣ ለክልሉ የሰላም እና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊነት እና ስልጣን ተሰጥቷል። የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጠቅላይ መመሪያ እዙ ጋር በመተባበር ይህ የሰላም ጥሪ ተግባራዊ ሆኖ በክልሉ ግጭት እና ሁከት እንዲቀር፣ሕዝብም እፎይታ እንዲያገኝ ያለውን ቁርጠኝነት እየገለጸ፤ ለዚህ ጥሪ ውጤታማነት አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ባለድርሻ አካላት ሁሉ፣በተለይም የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች ለሰላም አጀንዳው መሳካት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ መቅረቡን የኢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

በዚሁ አጋጣሚ ይህን ጥሪ ቸል በማለት የአመፅ እና የጉልበት መንገድ በሚመርጡ ግለሰቦች እና ታጣቂዎች ላይ የተጀመረው የሕግ ማስከበር እርምጃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም በመግለጫው ተገልጿል፡፡

## የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ የነበረው ታየ ደንደአ በሕግ ቁጥጥር ሥር ዋለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ የነበረው ታየ ደንደአ በሕግ ቁጥጥር ሥር መዋሉን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል አስታወቀ፡፡

ግብረ ኃይሉ ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በሕግ ቁጥጥር ስር የዋለው የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ የነበረው ታየ ደንደአ፤ ከለውጡ በፊት የኦነግ አባል የነበረና በእስር ቤት የቆየ ሲሆን፤ የለውጡ መንግሥት ባደረገለት ምህረት ከማረሚያ ቤት ተለቆ በተሰጠው እድል በተለያዩ የክልል እና የፌዴራል መንግሥት የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሲሠራ ነበር ብሏል።

ይሁን እንጂ ታየ ደንደአ ከሕዝብና ከመንግሥት የተሰጠውን ኃላፊነት በተለይም ደግሞ የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ ሆኖ ሰላምን ለማስፈን መሥራት ሲገባው፤ በተቃራኒው ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከሚንቀሳቀሱ ፀረ ሰላም ኃይሎች ጋር በመተሳሰር ለጥፋት ተልዕኮ በህቡዕ ሲሠራ ተደርሶበታል ብሏል መግለጫው።

መግለጫው አያይዞም በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በንፁሃን ዜጎች ላይ ሲፈፀሙ በነበሩ የሽብር ተግባራት በተለይም ደግሞ ከእገታ ጋር በተያያዘ እጁ እንደአለበት የተደረሰበት መሆኑን አስታውቋል።

ይህንን እኩይ ዓላማ ሲያራምድ የነበረው ተጠርጣሪ ታየ ደንደአ፤ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሊውል እንደሚችል ሲገምት ታጋይ ለመምሰል በራሱና በተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ ትስስር ገፆች አፍራሽና ፀረ ሰላም ፅሑፎችን፣ ንግግሮችንና መግለጫዎችን በማን አለብኝነት ሲያስተላልፍና ሲሰጥ ቢቆይም ከተጠያቂነት ማምለጥ ባለመቻሉ በጋራ ግብረ ኃይሉ በቁጥጥር ስር መዋሉን መግለጫው አመልክቷል።

በተጨማሪም የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል ለመገናኛ ብዙኃን በላከው መግለጫ እንደገለጸው፤ ታየ ደንደአ መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ተቀብሎ እየሰራ በነበረበት ወቅት መንግሥታዊና የፓርቲ መዋቅሩን በሴራ ለመናድ በህቡእ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መቆየቱን በመረዳት ያላሰለሰ ጥናትና ክትትል ሲደረግበት ነበር ብሏል፡፡

በተደረገው ክትትልም ታየ ደንደአ ከሸኔ አመራሮችና በሽብር ወንጀል ከተጠረጠሩ ጽንፈኛ ኃይሎች ጋር ትስስር



በመፍጠር መንግሥትን በአመጽ፣ በሽብርና፣ በትጥቅ ትግል ለመጣል ሲያሴር እንደተደረሰበት መግለጫው ጠቁሟል፡፡

ተጠርጣሪው ታየ ደንደአ በሕግ ቁጥጥር ሥር በዋለበት ወቅትም በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ በተደረገ ፍተሻ፤ ግለሰቡ በህቡዕ ለሚያደርገው ፀረ-ሰላም እንቅስቃሴ ሲገለገልባቸው የነበሩ የተለያዩ 9 ሞባይሎች፣ 4 ላፕቶፖች፣ 3 አይፖዶች፣ በርካታ ፍላሾች፣ 2 የፊትና የኋላ የተለያዩ ተሽከርካሪ ሰሌዳዎች እና ልዩ ልዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች፣ ክላሽንኮቭ ጠመንጃና ሽጉጦች ከመሰል ጥይቶች ጋር እንዲሁም የኦነግ ሸኔ አርማዎችና በተለያዩ ግለሰቦች ስም የተዘጋጁ የኦነግ ሸኔ መታወቂያዎች፣ ሰነዶችና ማስታወሻዎች እንደተገኙ ግብረ-ኃይሉ በላከው መግለጫ አረጋግጧል፡፡

ከዚህም ባሻገር በብርበራ ወቅት በመኖሪያ ቤት ውስጥ በሦስት መታወቂያዎች የሚጠቀም አንድ የኦነግ ሸኔ አባል ተደብቆ መገኘቱንና በቁጥጥር ሥር መዋሉንም መግለጫው ጨምሮ ገልጿል።

ታየ ደንደአ በተመደበበት ከፍተኛ የመንግሥት ስልጣን ላይ ሆኖ በተደጋጋሚ መንግሥትን ገዳይና ጨፍጫፊ እያለ ሲወቅስ የሚደመጥ ቢሆንም፤ በተግባር ግን ከሽብርተኞች፣ ጽንፈኞችና ነፍሰ ገዳዮች ጋር የጥፋት ትስስር የነበረው ራሱ መሆኑ በተደረገ ክትትል መረጋገጡን የጋራ ግብረ ኃይሉ መግለጫ ጠቁሟል።

በመጨረሻም በመንግሥትና በፓርቲ መዋቅር ውስጥ ሆነው በተመሳሳይ እኩይ ዓላማ በተሰማሩ አካላት ላይ በጥናት የተመሰረተ ጥብቅ ክትትል የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል እያደረገባቸው እንደሚገኝና እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰዱ ሕጋዊ እርምጃዎችን በተከታታይ ለሕዝብ ይፋ የሚያደርግ መሆኑን መግለጫው አስታውቋል።

## የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋሙ ሥራ እንዲሳካ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋሙ ሥራ እንዲሳካ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው ብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን ገለጸ፡፡

በቀድሞ ተዋጊዎች ዲሞቢላይዜሽንና መልሶ ማቋቋምን በሚመለከት የፖለቲካ ፓርቲዎች ባላቸው ሚና ላይ ያተኮረ ውይይት ትናንት ተደርጓል።

በውይይቱ ላይ የብሔራዊ ተሀድሶ ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ መንግሥት የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ ለማቋቋም ተቋም አቋቁሞ እየሰራ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህ ፕሮግራም ሊሳካ የሚችለው የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሲኖር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽኑ ከተለያዩ አካላት ጋር ውይይት ሲያደርግ መቆየቱንም አውስተው ከክልል መንግሥታት ፣ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ከሚዲያ አካላት ፣ከግሉ ሴክተር፣ከተለያዩ መንግሥት ተቋማት እና ከልማት አጋሮች ጋር ውይይት መደረጉንም ጠቁመዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች በሀገር ጉዳይ ላይ አንድ ባለድርሻ አካል መሆናቸውን የተናገሩት አምባሳደሩ፤ ፓርቲዎቹ የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋሙን ሥራ አስፈላጊነትና ፋይዳ በመረዳትና ለአባላቶቻቸው ግልጽ በማድረግ ለሰላም ግንባታ አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸው ገልጸዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰላም እንዲጸና እና ጦርነት እንዲቆም በዋናነት “የአድቮኬሲ” ሥራ እንዲሰሩ እንደሚፈለግ የጠቆሙት አምባሳደር ተሾመ፤ ፓርቲዎች የተለያየ የፖለቲካ አስተሳሰብ ቢኖራቸውም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህል እንዲዳብር ከራሳቸው አባላቶች ጀምሮ ቢሠሩ ለኮሚሽኑ ትልቅ አስተዋጽኦ መሆኑን አስረድተዋል።

የቀድሞተዋጊዎቹመልሶመደራጀቱንእንደሚፈልጉት ተናግረው፤ የዝግጅት ምዕራፍ ሥራው በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይሄድ አዳጋች ሁኔታዎች መኖራቸውን



**አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**

ተናግረዋል፡፡ ለዚህ ፕሮጀክት የሚያስፈልገው ፋይናንስ ከፍተኛ መሆንም አንዱ ተግዳሮት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የዝግጅት ምዕራፉ በተለያዩ መመዘኛዎች ሲለካ የዘገየ እንዳልሆነ የሚናገሩት አምባሳደር ተሾመ፤ ኮሚሽኑ ሥራውን በተቻለ ፍጥነት ማከናወን የሚፈልግ በመሆኑ በሚታሰበው ፍጥነት መሄድ አለመቻልን እንደተግዳሮት እንደሚታይ አስረድተዋል፡፡

ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በሚቀጥለው በፈረንጆቹ 2024 ከአጋር አካላት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ አመላክተው፤ ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም ሁሉም አጋር አካላት የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ ባቀረበው መሰረት ድጋፍ መደረግ መጀመሩን ጠቁመዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ወይዘሮ ደስታ ጥላሁን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የታጠቁ አካላት ትጥቃቸውን ፈትተው ወደ ውይይት እንዲመጡ የጋራ ምክር ቤቱ “የአድቮኬሲ” ሥራ ይሠራል።

በመድረኩ ኮሚሽኑ እንደመጀመሪያ በፈረንጆቹ 2024 ከትግራይ ክልል 50ሺ የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ ለማደራጀት እየሠራ መሆኑ ተገልጿል።

በውይይቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# በአማራ ክልል ከተሞች 44 ሺህ ቤቶች ይገነባሉ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በበተያዘው በጀት ዓመት በአማራ ክልል በሚገኙ ከተሞች የነዋሪዎችን የቤት ችግር ለመቅረፍ 44 ሺህ ቤቶች እንደሚገነቡ የክልሉ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር መዓረግ የአማራ ክልል ከተሞች ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪና የከተማ መሰረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ አህመዲን ሙሀመድ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤በተያዘው በጀት ዓመት በክልሉ በሚገኙ ከተሞች የነዋሪዎችን የቤት ችግር ለመቅረፍ 44 ሺህ ቤቶች ይገነባሉ፡፡

እንደ አህመዲን (ዶ/ር) ገለጻ፤ ቤቶቹ በሪልስቴት፣በማህበራት በማደራጀት፣ ለግለሰቦች የቤት መስሪያ ቦታ በመስጠት እንዲሁም በመንግሥት የሚገነቡ ናቸው፡፡

ከከተሞች ማደግ ጋር ተያያዞ የሚፈጠሩ ችግሮች በአግባቡ መምራትና መግራት ካልተቻለ ብዙ ጉዳቶች አሉት፤ ከዚህም አንዱ የነዋሪዎች የቤት እጦት ችግር ዋነኛው ነው፡፡

በከተሞች የመኖሪያ ቤት አቅርቦት መሰረታዊ ችግር ነው ያሉት ዶክተር አህመዲን፤ በክልሉ በሚገኙ ከተሞች ያለውን የቤት አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ ፈጣን የሆኑ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በአጭር ጊዜ ተገንብተው ለነዋሪዎች እንዲተላለፉ ታቅዶ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ዶክተር አህመዲን አክለውም፤ የሚገነቡት ቤቶች በታቀደላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለቤት መስሪያ ግብዓት ከማሟላት አንጻር ሰፋፊ ስራዎች እየተሰሩ ነው ያሉ ሲሆን፤ በተጨማሪም ለቤት ግብዓት የሚሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች እየተገነቡ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ጎንደርና ባህርዳር ከተሞች ላይ ፈጣን የኮንክሪት ማምረቻ ቴክኖሎጂ እንዲሁም ደብረብርሃን ከተማ ላይም ለቤት ግንባታ የሚውል ካናል ማምረት የሚያስችል ኢንዱስትሪ ወደ ሥራ ገብቷል ያሉት አህመዲን (ዶ/ር)፤ እነዚህን ጅምር ተግባራት ወደ ውጤት መቀየር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡


አህመዲን ሙሀመድ(ዶ/ር)

በክልሉ ለቤት መስሪያ ብለው ወስደው ለተለያየ አገልግሎት በሚያውሉ አካላት ላይ ክትትል እንደሚደረግም ነው ዶክተር አህመዲን የገለጹት፡፡

የቤት ግንባታ ጋር ተያይዞ የራሱ የአሰራር መመሪያ ይፈልጋል፤ ይንንም በሚመለከት የአሰራር ሥርዓት እየተዘጋጀ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አህመዲን (ዶ/ር) ገለጻ፤ በክልሉ ስምንት የ"ጂኦ ፖሉታንት" ከተሞች አሉ ያሉ ሲሆን፤ በከተሞቹ የነገውን ትውልድ ጥቅም የሚያስከብርና ለአደጋ የማያጋልጥ ስትራቴጂክ እቅድ እየተዘጋጀ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በስምንቱ ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ሲዘጋጅ ቴክኖሎጂ፣ ዲጂታላዜሽን እንዲሁም ስማርት ሲቲን ታሳቢ ያደረገ ሥራ እንዲሰሩ የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

በከተሞቹ የነዋሪውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍ የመሰረተ ልማት ስራዎች የተሟሉ እንዲሆኑ በተለይ የመንገድ መሰረተ ልማቶች በተለመደው መስራት ብቻ ሳይሆን ቴክኖሎጂን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ባህርዳር፣ ደብረብርሃን፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ወልዲያ፣ ደብረታቦር፣ ደብረማርቆስና ኮምቦልቻ በክልሉ ወደ "ስማርት ሲቲነት" ከሚያድጉ ከተሞች መካከል ናቸው፡፡

## ለዓባይ ግድብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደተለመደው ሕዝቡ በነቂስ ለግድቡ ድጋፍ እየተሳተፈ አይደለም ብለዋል፡፡

ይህም ሆኖ ለግድቡ ማጠናቀቂያ እየተሰበሰበ ያለው ገቢ ከፍተኛ ነው፤ ግጭቱ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል ለማለት አያስችልም ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ከዲያስፖራውና ከማህብረሰቡ እየተሰበሰበ ያለው የግድቡ ማጠናቀቂያ የገንዘብ ድጋፍ ከዓመት ዓመት እየጨመረ ነው ብለዋል፡፡

በክልሎች ለዓባይ ግድብ ገቢ የማሰባሰቢያ ንቅናቄ በተጠናከረ መልኩ እየተሰራበት መሆኑን ገልጸው፤ ዲያስፖራውም የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ለዓባይ ግድብ ግንባታ ገቢ ማሰባሰብብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶም ከ18 ቢሊዮን ብር በላይ ከኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ተሰብስቧል ብለዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 383 ሚሊዮን 213 ሺህ በላይ ብር መሰብሰቡን የተናገሩት ኃላፊው፤ በሲዳማ ክልል ለዓባይ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከ108 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን አብራርተዋል፡፡

አቶ ሀይሉ አያይዘውም ግድቡ ከተጀመረ እስካሁን 170 ቢሊዮን ብር የፈጀ ሲሆን፤ ግንባታው ከ90 በመቶ በላይ ደርሷል፤ ለማጠናቀቅም 60 ቢሊዮን ብር ገደማ ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

## ባንኩ ኢትዮጵያ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዶክተር አያሌው ገልጸው፤ በዚህም ዘርፉን ለማዘመን በወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ 15 ትራክተሮች፣ በሞኢንኮ ኢንተርናሽናል 10 ማጨጃ እና መውቂያ ወይም የኮምባይን ሀርቨስተር ማሽኖች እንዲሁም በቢሾፍቱ ሐግቤህ 14 ኤክስካቫተሮችን አስረክቧል።

ባንኩ ከሚተገብራቸው አገልግሎቶች ውስጥ የሚጠቀሰው የሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ሲሆን ደንበኞች 20 በመቶ ተቀማጭ በማድረግ 80 በመቶ በባንኩ ተሸፍኖላቸው የተለያዩ ማሽኖችን እንዲገዙ የሚደረግበት ነው፡፡ ለዚህም በአጠቃላይ 203 ሚሊዮን 551 ሺህ በላይ ወጪ መደረጉን አስታውቀዋል።

ባንኩ ያስረከባቸው ማሽኖች በዘርፉ የተሰማሩትን አካላት ጊዜ እና ወጪ ከመቆጠብ ባለፈ የምርት ብክነትን የሚቀንስ እና ከዘርፉ የሚገኘውን ምርታማነትን የሚጨምር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እስካሁን ድረስ በግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ 5 መቶ 86 በላይ የግብርና መሳሪያዎችን በማቅረብ 4 መቶ 62 ደንበኞችን ተጠቃሚ ያደረገ መሆኑን ዶክተር አያሌው አስታውቀዋል፡፡

እንዲሁም በማእድኑ ዘርፍ በአሁኑ ወቅት በ1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር 89 ደንበኞች የተለያዩ ማሽኖችን በማስረከብ ተጠቃሚ ያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል። በቀጣይም ባንኩ 16 ኤክስካቫተሮችን ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ እንደሚያስረክብ አስታውቀዋል፡፡

ማሽኖቹ ሥራን በማቀላጠፍ ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው እና ለሰፊ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሥራ እድል የሚፈጥሩ እንደሚሆኑ አስታውቀዋል፡፡ በዚህም የሀገሪቱን የግብርና እና ማእድን ዘርፍ በማዘመን አምራቹን በዘርፉ እንዲሰማራ በማድረግ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ይገባል ብለዋል፡፡

# በአዲስ አበባ 70 በመቶ የሚሆነው የኃይል መቆራረጥ የሚያጋጥመው በዛፎች ምክንያት ነው

### - አገልግሎቱ በ121 ሠራተኞቹ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ወሰደ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ 70 በመቶ የሚሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ የሚያጋጥመው በዛፎች ምክንያት መሆኑን የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡ አገልግሎቱ ባለፈው በጀት ዓመት ህገወጥ ተግባር ላይ በተሰማሩ 121 ሰራተኞቹ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ወስዷል፡፡

የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ገበየሁ ሊካሳ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ኔትወርክ እንዲቆራረጥ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች ውስጥ ዛፎች ቀዳሚ ናቸው፡፡ ከሚቆራረጠው ኃይል ውስጥ 70 ከመቶው የሚሆነው ዋናው ኤሌክትሪክ በዛፎች ምክንያት ከመሬት ጋር ሲነካካ የሚከሰት ነው፡፡

ዛፎችን ለመቁረጥ ፈተናው ከባድ ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ይቆረጡ ሲባል ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጩኸት ይመጣል፡፡ ለምሳሌ የከተማው አረንጓዴ ልማትና ውበት ዛፎችን አልምቶ ለደረሱበት ደረጃ ብዙ ዘመን እንደወሰደበት በመግለጽ እንዳይቆረጡ የሚከለከልበት ሁኔታ አለ፡፡ ዝናብና ነፋስ ሲኖር ዛፎች ከመስመሩ ጋር ስለሚገናኙ የኃይል መቆራረጥ ያጋጥማል ብለዋል፡፡

እንደ ገበየሁ (ዶ/ር) ገለጻ፤ በጀት ዓመቱ በዛፎች ሳቢያ የሚከሰተውን የኃይል መቆራረጥ ለማስተካከል ከአረንጓዴና ከተማ ውበት እና ከሌሎች የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር ምክክር እየተደረገ ነው፡፡ በዚህም በተወሰኑ ጉዳዮች ስምምነት ላይ ተደርሶ የሚከታተልና ትምህርት የሚሰጥ ባለሙያ በ«የሳይቶች» ተመድበው ዛፎ እንዲቆረጡ ውይይት እየተደረገ ነው፡፡ ሆኖም በመሰረታዊነት ለውጥ የሚመጣው ዛፎችን በመቁረጥ ነው ብለዋል፡፡

መመሪያው የኤሌክትሪክ ኔትወርክ ከተዘረጋበት በግራም በቀኝም አምስት ሜትር "ራዲየስ" ውስጥ ዛፍ መኖር የለበትም የሚል መሆኑን የጠቆሙት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ነገር ግን በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ አልተደረገም ብለዋል፡፡

አሁን አጠቃላይ ወደ ሰባት ሺ ኪሎ ሜትር በከተማ አስተዳደሩ መስመሮች አሉ፡፡ ከሰባት ሺ ኪሎ ሜትር ውስጥ ከፍተኛ መስመር የሚባለው ሁለት ሺ 200 ኪሎሜትር ሲሆን በዛፎች ጉዳት እየደረሰበት ያለውም ይኸው መስመር ነው ብለዋል፡፡

ከባለድርሻ አካላት ጋር ዛፎች በተገቢው ቦታ እንዲተከሉና በኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥሩ ለማስቻል የጋራ እቅድ እየታቀደ እንደሆነም ገበየሁ (ዶ/ር) ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል ተቋሙ በተለያዩ ደረጃዎች ህገወጥ ተግባር ላይ በተሰማሩ 121 ሰራተኞቹ ላይ እርምጃዎች መውሰዱንም ገበየሁ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

በአገልግሎት መስሪያ ቤቱ 44 በመቶ የሚሆነው ሙስና አዳዲስ ደንበኞችን ከማስተናገድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እርምጃ የሚወሰድባቸው ሰራተኞች 44 ከመቶ የሚሆኑት ከአዲስ ደንበኛ ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ ከገማች እስከ ቆጣሪ ለጣፊው ድረስ በስነ ምግባር ማሻሻያ፤ በምክርና በሌሎች ክትትሎች ከአላስፈላጊ ድርጊታቸው ባልታቀቡ ሰራተኞች ላይ እርምጃ ይወሰዳል ብለዋል፡፡

ባለፈው 2015 በጀት አመት ላይ 121 ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዷል፡፡ እርምጃው ከማስጠንቀቂያ፤ ደመወዝ ማገድ እስከ ከሥራ ስንብት የደረሰ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፡፡ ህብረተሰቡ ብልሹ አሰራሮችን ጥቆማ የሚሰጥበት ዌብሳይት እየበለጸገ ስለሆነ በከፍተኛ ደረጃ ብልሹ አሰራር የሚቃለልበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል፡፡

በዚህና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ገበየሁ ሊካሳ (ዶ/ር) ጋር ያደረግነው ሙሉ ቃለ ምልልስ በተጠየቅ አምዳችን ላይ ያገኙታል፡፡



## በክልሉ በ3 ነጥብ 1...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደመሆኑ እስከ አሁን 3ነጥብ1 ሚሊዮን ሄክታር ላይ የሚገኝና 62 ፐርሰንት የሚሆነው ምርት መሰብሰቡን ተናግረዋል፡፡

የኤክስፖርት ሰብሎች የሚባሉት እንደ ሰሊጥ ፣ማሾ እና ቦሎቄ ፈጥነው የሚደርሱ በመሆኑ 98 ፐርሰንት የሚሆነውን መሰብሰብ መቻሉን ጠቁመው፤ የኢንዱስትሪ ሰብሎች የሚባሉትን ስንዴ፣የቢራ ገብስና አኩሪ አተር ደግሞ 54 ፐርሰንት መሰብሰብ እንደተቻለ አመላክተዋል።

የምግብ ሰብሎች የሚባሉት እንደ ጤፍ፣ስንዴ፣ሩዝ እና በቆሎ 56 ፐርሰንት የሚሆነው እንደተሰበሰበ የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በጥቅል 62 ፐርሰንት የሚሆነው ምርት መሰብሰቡን ገልጸዋል፡፡

የባለፉት ሳምንታት የዝናቡ ሁኔታ ስጋት ፈጥሮ የነበረ በመሆኑ የደረሱ ሰብሎች በፍጥነት እንዲሰበሰቡ ቅስቀሳ ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመው፤ የዝናቡ ሁኔታ ጠንከር ብሎባቸው በነበሩ ቦታዎች ላይ ተማሪዎች፣የመንግሥት ሰራተኞች እና የጸጥታ መዋቅር አካላትን ጭምር በሰብል ስብሰባው ሂደት በማሳተፍ የደረሱ ሰብሎችን በፍጥነት መሰብሰብ መቻሉን አስረድተዋል፡፡

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንደ ኮምባይነር በመጠቀም የሰብል ስብሰባው መከናወኑን የተናገሩት አቶ ቃልኪዳን፤ የምርጥ ዘርና የምግብ ሰብሎችን ለማሰባሰብ በአጠቃላይ 29 ኮምባይነሮች ጥቅም ላይ እንደዋሉ ጠቁመዋል።የጥራጥሬ ሰብሎችን እንደ አኩሪ አተር ያሉትን ለመፈልፈል 272 ትሬሽሮች ጥቅም ላይ መዋላቸውንም ተናግረዋል፡፡

በመካናይዜሽን ሥራ በጥቅሉ 7ነጥብ1 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ማሰባሰብ መቻሉን የጠቆሙት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ እንደ ክልል ሁሉንም አማራጮች በመጠቀም የምርት ማሰባሰቡ ሂደት ተከናውኗል ብለዋል።

የምርት አሰባሰቡ ሂደት የሚጠናቀቅበት ጊዜ እንደ ሰብሉ እንደሚለያይ ተናግረው፤ የኤክስፖርት ሰብሎች ሰሊጥ፣ማሾና አኩሪ አተር የመድረሻ ጊዜያቸው ፈጣን በመሆኑ የመሰብሰቡ ሥራ በአብዛኛው መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

እስከ 90 ፐርሰንት የሚሆኑት ሰብሎች እስከ ታህሳስ መጨረሻ ተሰብስበው ይጠናቀቃሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የሚናገሩት አቶ ቃልኪዳን፤ ሁሉን በማሳ ላይ ያሉ ሰብሎች እስከ ጥር አጋማሽ ተሰብስበው እንደሚጠናቀቁ ጠቁመዋል፡፡ የምርት ማሰባሰቡ ሂደት ሲጠናቀቅም 160 ሚሊዮን ኩንታል ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል፡፡

በምርት ማሰባሰቡ ሂደት የዝናቡ ሁኔታ እና አሁን ያለው የክልሉ ሁኔታ የመካናይዜሽን መሳሪያዎችን ከቦታ ወደ ቦታ ለማንቀሳቀስ እንቅፋት ሆነው እንደነበር ተናግረው ሥራው በማቻቻል እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

አሁን ላይ በክልሉ ያለው የዝናብ ሁኔታ ለሰብል መሰብሰቡ ሥራ አመቺ እንደሆነ ተናግረው፤ ይሄ ሁኔታ ሊቀየር የሚችል በመሆኑ በክልሉ የሚገኙ አርሶአደሮች በማሳ ላይ ያሉ ሰብሎችን በፍጥነት እንዲሰበስቡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሀገር መከላከያ ሠራዊትን ስም በማጠልሸት ከተልዕኮው ማስቆም አይቻልም

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው፡፡ ከራሱ ሰላም አልፎም የጎረቤት ሀገራትን ሰላም የሚያስከብርና ወዳጅነትን አጥብቆ የሚፈልግ እንግዳ ተቀባይ ሕዝብ ነው፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት ከመሆኑም ባሻገር ልዩነቶችን ጌጥ አድርጎ የሚቀበልና አብሮነትን የሚያስቀድም ድንቅ ሕዝብ ነው፡፡

ሆኖም የዚህን ኩሩና ሰላም ወዳድ ሕዝብ አኩሪ ዕሴቶች ለማምከን የተለያዩ ሴራዎች በውስጥና በውጭ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ሕዝቡ የመከባበርና የመቻቻል ዕሴቱን እንዲያጣ በብሔርና ሃይማኖት በመከፋፈልና በማናቆር ግጭት እንዲነግስና በሂደትም የተዳከመች ኢትዮጵያ እንድትፈጠር በርካታ አካላት ያለመታከት ሠርተዋል፡፡ ዛሬም እንቅልፍ አጥተው እየሠሩ ነው፡፡

ዛሬ ዛሬ ከኢትዮጵያውያን ባህል ባፈነገጠ መልኩ ፍላጎታቸውን በነፍጥ ማሳካት የሚፈልጉ ቡድኖች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ ከውይይት ይልቅ ነፍጥ ማንሳት የሚቀናቸውና ሰላም ወዳዱን ሕዝብ የሚረብሹ፤አብሮነቱን የሚያውኩ ፤የኢትዮጵያን መረጋጋትና ሉአላዊነት የሚገዳደሩ ቡድኖች እዚህም እዚያም አቆጥቁጠዋል፡፡

እነዚህ ወገኖች በሚፈጥሩት ሁከትና ብጥብጥም ልማት ተደናቅፏል፤የሰዎች ወጥቶ መግባት ተስተጓጉሏል፤አለፍ ሲልም የሀገር ህልውናም አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣በቤኒሻንጉልና በጋምቤላ አንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው ሃቅም ይኸው ነው፡፡

የእነዚህን የግጭት ነጋዴዎች ሴራ ለማምከንና ብሎም አደብ ለማስገዛት ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት ሕይወቱን ጭምር በመገበር ሌት ተቀን እየሠራ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የጀግንነት መገለጫ ጥግ ነው፡፡ ሠራዊቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የወጣ በመሆኑ እራሱን ለሕዝብና ለሀገር አሳልፎ ይሰጣል፤ የሀገሪቱን ሉአላዊነትን ለማስከበርና የዜጎችን ሰላም ለማረጋገጥ መስዋዕትነትን ይከፍላል፡፡ በዱር በገደሉ ይዋደቃል፡፡ደሙን ያፈሳል፤አጥንቱን ይከሰክሳል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በጀግንነቱ ሁሉም በአንድ ድምጽ የሚስማማበት በሰላም ጊዜ የልማት አርበኛ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር ጀግና ሠራዊት ነው፡፡ ሠራዊቱ ድል የሚፈጥር፣ ሞትን የሚያሸንፍ፣ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር፣ ፍላጎቱን ለአላማው የሚያስገዛ፣ የነፃነትን ዋጋ ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ጨለማን ማሻገር የሚችል ልበ ሙሉ ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በሰላም ጊዜ የልማት አርበኛ በጦርነት ወቅት ጀግና ሆኖ በስኬት በመራመድ ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሀገሩን ዳር ድንበር ከማስከበሩም ባሻገር በጎረቤት ሀገራት ጭምር ተልዕኮ በመውሰድ ሰላምን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡ በሶማሊያ፤በሱዳን፤ቀደም ሲልም በላይቤሪያ፤በሩዋንዳና ቡሩንዲ ሀገራት ተሰማርቶ ሰላም ማስከበር የቻለ የሕዝብ ልጅ ነው፡፡ ይህም ብቃት ሊገኝ የቻለው ከሠራዊቱ ተፈጥሯዊ ባህሪ በሻገር በየጊዜው እየተደረገለት በመጣው አቅም ግንባታ ሥራዎች አማካኝነት ነው፡፡

በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት ሠራዊቱን ለማዘመን በተሠሩ የለውጥ ሥራዎች የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ እራሱን በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ በማጠናከር ሳይዋጋ የሚያሸንፍበት ብቃት ላይ ደርሷል፡፡

የምድር ኃይልን በሰው ኃይልና የውጊያ አፈጻጸም በማጎልበት ከአየር ኃይልና ከሌሎች አቅሞች ጋር ያለውን ቅንጅት የማሳደግ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በትጥቅና በመረጃ ግንኙነት አቅሙን በመገንባትም የማሸነፍ ብቃቱን አሳድጓል፡፡ ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲና ከተለያዩ የደህንነትና የጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት የባህር ኃይልን አቅም የማሳደግና የሳይበር ጥቃት ዝግጁነት /የሳይበር ዋርፌር/ ብቃትን በማሳደግ ከተለመደው የውጊያ ስልት ወጣ በማለት የሚቃጡ ዘመን አመጣሽ ጥቃቶችን የመከላከል ብቃቶችን ተጎናጽፏል፡፡

መከላከያ ከለውጡ ወዲህ በሠራቸው የሪፎርም ሥራዎች በቴክኖሎጂ አቅም ማሳደግ፣ በመከላከያ ምርምር ሥራዎች፣ በባህር ኃይል ዝግጁነትና ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አከናውኗል፡፡በሀገር ውስጥና በውጭ አገራት የተቃጡ ውስብስብ ጥቃቶችን የመመከት ብቃቶችን አዳብሯል፡፡

ሆኖም የመከላከያ ሠራዊት መጠናከር ስጋት የሚሆንባቸውና ሴራቸውንም እንደሚያመክንባቸው ያወቁ ቡድኖችና ግለሰቦች ግብረ አበሮቻቸውን ሰብስበው በሰፊው ስም የማጥፋት ዘመቻ ውስጥ ይገባሉ፡፡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ለብሶ ታላላቅ ድሎችን የተጎናፀፈውን ጀግና የመከላከያ ሠራዊታችንንም ስም በማጠልሸት ኢትዮጵያን ለማሳነስም በቀቢጸ ተስፋ ሲሯሯጡ ታይተዋል፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት በወሬ የማይፈታ እና ለአፍታም ቢሆን በአሉባልታ የማይበገር መሆኑን ማመን ይገባል፡፡ሰላምን በማወክ ከግጭት ማትረፍ የሚፈልጉ አካላትም አዋጪው ሰላምና ፤ሰላም ብቻ መሆኑን መረዳት ይገባቸዋል፡፡


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሰማዩ ለብርቱዎች ብቻ ነው - የኢትዮጵያ አየር ኃይል

ወርቁ ማሩ

ስሙ ከሀገር አልፎ በአፍሪካ የገነነ ነው። ጠጋ ብለው ሲመለከቱት ደግሞ ለኢትዮጵያ የሚመጥን ትልቅ ተቋም ስለመሆኑ በተግባር ያረጋግጣሉ፡፡ ከዚህም አልፎ የሀገር ግንባታ ሂደቱ ምን ያህል የላቀ ደረጃ ላይ እንዳለ ይረዳሉ። የለውጡ መንግሥት ከልማት ሥራውም ጎን ለጎን ሀገርን ከማንኛውም ጠላት ለመከላከል የሚያስችል አቅም መፍጠሩንም ይገነዘባሉ፡፡ ይህ ተቋም የኢትዮጵያ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አንዱ ክንፍ የሆነው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ነው፡፡

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከህዳር 20 ጀምሮ 88ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን በልዩ ልዩ መርሀ ግብሮች እያከበረ ይገኛል፡፡ ታህሳስ አራት፣ አምስትና ስድስት ደግሞ የበዓሉ አካል የሆኑ ልዩ ልዩ ሁነቶች ይከናወናሉ፡፡ ይህንንም መነሻ በማድረግ ሰሞኑን ከተለያዩ የሚዲያ ተቋማት የተውጣጣን የሚዲያ ባለሙያዎች ተቋሙን ለመጎብኘት እድል አግኝተናል። እኔም በጉብኝቱ ካየኋቸው በርካታ የተቋሙ ስኬቶች ጥቂቱን ላካፍላችሁ ወደድኩ፡፡

በርግጥ ስለዚህ ተቋም በዚህ አጭር ጽሁፍ ቀርቶ መጽሀፍም ቢጻፍ በልኩ ማስረዳት ይቻላል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ምክንያቱም ተቋሙ የተገነባበት መንገድ ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ሆኖም ግን በጥቂቱ እንካችሁ፡፡

የኢትዮያ አየር ኃይል ትልቅነት የሚታየው ገና ከበሩ ሲገቡ ጀምሮ ነው፡፡ የበሩ መግቢያ ላይ አንድ ጽሁፍ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ “The sky is only for strong person” በግርድፉ ሰማዩ ለብርቱዎች ብቻ ነው፡፡ የሚል ስያሜን ሊይዝ ይችላል፡፡ ይህ ጽሁፍ ተቋሙንና የተቋሙን ሠራተኞች በትክክል የሚገልጽ መሆኑን ለመረዳት ታዲያ ወደ ውስጥ ዘልቀው ስለተቋሙ ጥቂት ማየት ብቻ በቂ ነው፡፡

ከዋናው በር ወደ ውስጥ ሲዘልቁ በግራና በቀኝ የተዋበ ሥፍራ ያገኛሉ፡፡ ይህ ሥፍራ ታዲያ ዝም ብሎ ለአረንጓዴ ስፍራነት ብቻ የተቀመጠ አይደለም። ልዩ ልዩ አትክልቶች ይመረቱበታል። ከጎመን ጀምሮ ቆስጣና ሰላጣ፣ አበባዎች እና ሌሎች አትክልቶች በልዩ እንክብካቤ በአንድ በኩል ለምግብነት ሊውሉ፤ በሌላ በኩል አካባቢውን በልምላሜ ሊያደምቁ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

አዲስ ወደዚህ ተቋም የገባ እንግዳ በዚህ ሥፍራ ጥቂት አረፍ ቢል ምኞቱ እንደሚሆን ከራሴም ፍላጎት መረዳት ችያለሁ፡፡ ይህ ግን ለጥቂት ደቂቃ ብቻ የሚቆይ ስሜት ነው፡፡ ምክንያቱም ወደውስጥ ሲዘልቁ ብዙ ለዓይንና ለውስጣዊ ስሜት ርካታን የሚያጎናጽፉ በርካታ ጉዳዮች አሉና፡፡

ትንሽ ሄድ ሲሉ አንድ በእንክብካቤ የተያዘ የእግር ኳስ ሜዳ ያገኛሉ፡፡ በርግጥ ይህ ሜዳ ከጥቂት ዓመታት በፊት ያልነበረ አዲስ የሪፎርሙ ትሩፋት ነው፡፡ ለጊቢው ግን ልዩ ውበት ከማጎናጸፉም በላይ ወታደር ለስፖርት ቅርብ መሆኑን ያሳያል፡፡ እኛም እንዲህ እንዲህ እያልን አንዱን አይተን ሳንጠግብ ሌላ ከዚያ የማይተናስ ውበት እያየን ወደ ውስጥ መዝለቃችንን ተያያዝነው፡፡

በቅድሚያም የተለያዩ የውግያና ሌሎች ወታደራዊ አውሮፕላኖች እንዲሁም ለልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ቪአይፒ አውሮፕላኖች በረራ ሲያደርጉም ተመለከትን፡፡ የሄሊኮፕተሮቹ እሽክርክሪት፤ ከሩቅ ይገፋተራል፤ የጀቶቹ ድምጽ ደግሞ የውስጥ ስሜት ያርዳል፤ በአጠቃላይ እዚያ አካባቢ ያለው ድባብ አስፈሪም፣ ግርማ ሞገስ ያለው ነው።

አውሮፕላኖቹን ከማብረር ጀምሮ ሁሉንም የግንኙነት ሥራዎችና አጠቃላይ የቁጥጥር ሥራውን ያለምንም የውጭ ዜጋ ጣልቃገብነት የሚያከናውት ኢትዮያውያን ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ሲታይ የአየር ኃይላችን በሰው ኃይል ልማት የደረሰበትን የእድገት ደረጃ መረዳት ያስችላል፡፡

የአየር ኃይል ዋና አዛዥ የሆኑት ሌተና ጄኔራል ይልማ መርዳሳ ለበዓሉ መሳካት የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን እየጎበኙ መመሪያዎችን በመስጠትና በማስተካከል ተጠምደዋል፡፡ በተለይ ታህሳስ 4፣5 እና 6 የሚከበረው በዓል ስኬታማ ይሆን ዘንድ ከወዲሁ ምን ተሠራ፣ ምን ይቀራል፤ የሚለውን ጉዳይ ከመደበኛ ሥራቸው ጎን ለጎን አንድ በአንድ ይከታተላሉ፡፡

ይህን የሚያክል ትልቅ ተቋም እንኳን መምራት መጎብኘትና ማወቅም ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለሚገነዘብ ሰው ሥራቸው ምን ያህል እረፍት አልባ እንደሚሆን ለመገመት አይከብደውም፡፡ ያም ሆኖ ግን ካላቸው ጥቂት ጊዜ ቀንሰው ስለበዓሉ ጥቂት ነገር ሊነግሩን ተቀላቀሉን፡፡

ሌተናል ጄኔራል ይልማ እንደሚሉት ፤የኢትዮጵያ አየር ኃይል የአንድ ትውልድ ወይም የአንድ ዘመን ሀብት አይደለም፡፡ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚገነባ ትልቅ ተቋም ነው፡፡ ስለዚህ ሀገርን የሚወክል እንዲህ አይነት ተቋም በየትኛውም ዘመን ቢሆን የራሱን ዐሻራ ትቶ ያልፋል፡፡

ታሪክ እየቆጠሩ የመከላከያን አልያም የአየር ኃይልን ታሪክ ማክበር ተገቢ እንዳልሆነ ፤ ከዚህ ቀደም አየር ኃይል በተለያዩ ወቅቶች በዓል ማክበሩን፤ አከባበሩ ግን የተቋሙን ታሪክ በሚገልጽ እና ተቋሙን በሚመጥን መልኩ አለመከበሩን፤ ችግሩን ለመፍታት የአየር ኃይል ቀን መቼ ይከበር የሚለው ውይይት እና ጥናት መጠየቁን አመላክተውናል፡፡ በዚህ መሠረት የቀደሙ የአየር ኃሃይል አባላትን ያካተተ እና በርካታ ባለሙያዎች የተሳተፉበት ኮሚቴ በማዋቀር ቀኑ መቼ ይሁን የሚለው መጠናቱን ጠቅሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር ኃይል በምስረታው አካባቢ የሰማይ ባቡር በሚል ስያሜ በውጭ ሀገር ዜጎች ሲመራ እንደነበር ጠቅሰው ፤ተቋሙ አሁን የያዘውን ስያሜ የያዘውና የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አዛዥ የተሾመለትን እለት ታሳቢ በማድረግ በዓሉ በየዓመቱ ህዳር 20 እንዲከበር መወሰኑን ገልጸውልናል፡፡

### ተቋሙ በየዘመኑ የነበረበት ሁኔታ

ሌተና ጄኔራል ይልማ እንደገለጹት ፤ተቋሙ ቀደም ሲል ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ ሂደቶች ውስጥ ነው ያለፈው፡፡ በነዚህ ሁሉ ሂደቶች ውስጥ የየራሱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ነበሩት፡፡ አንዴ ከፍ ሌላ ጊዜ ዝቅ ሲል ቆይቶ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ግን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እንዲያልፍ ግድ ብሎታል፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝ በነበረው ላይ ጨምሮ ተቋሙን ከማዘመን ይልቅ እያፈረሰ ከዜሮ መጀመር በመምረጡ በርካታ ተጀምረው የነበሩ መልካም ሥራዎች ወደኋላ እንደተመለሱ የአየር ሥይል የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ ካፒቴን ሻለቃ ሰይድ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ በወቅቱ ተቋሙ ከሥልጣና አንፃር ጀምሮ የነበረው ጥረት ተጠናክሮ ቢቀጥል ኖሮ ተቋሙ አሁን ከደረሰበትም ደረጃ በብዙ እጥፍ ማደግ ይችል እንደነበር በቁጭት

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ተጠየቅ

# "በ2015 በጀት ዓመት 121 ሠራተኞች ላይ ርምጃ ተወስዷል"

**ገበየሁ ሊካሳ (ዶ/ር)**
**የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ**


ፎቶ በአዩብ ተፈሪ

**ሞገስ ተስፋ**

ዛሬ ላይ ከዘመናዊነት ጋር ተያይዞም ይሁን በሌሎች አስገዳጅ ምክንያቶች በከተሞች አካባቢ የኤሌክትሪክ ኃይል በእጅጉ መሠረታዊ ጉዳይ ነው:: ለአብነት፣ በመዲናችን አዲስ አበባ ሁሉም ሥራዎች ከኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው:: በመኖሪያ ቤት ካሉ የማብሰያና መገልገያ እቃዎች እስከ ግዙፍ ፋብሪካዎች ድረስ የሚንቀሳቀሱት በኤሌክትሪክ ኃይል ነው::

የእንዳንዱ ህብረተሰብ ሕይወት ከኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ከመሆኑም አኳያ፤ ማህበረሰቡ «ዕራት እና መብራት አይንሳችሁ» በሚለው ብሂሉ የመብራትን አስፈላጊነት ይገልጸዋል:: ስለዚህም የኤሌክትሪክ አቅርቦቱ ለአፍታም እንዲቆራረጥበት አይሻም::

ይሁን እንጂ በከተማ አስተዳደሩ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኃይል መቆራረጥ ምክንያት የሚታዩ ችግሮች ስለመኖራቸው ለማስረዳት እማኝ መጥቀስ አያሻም:: በዚህም በሕዝብ ላይ ከሚያሳድረው ጫና ባሻገር፣ በሌሎች መሠረተ ልማቶች ጉዳት የሚያደርስበት አጋጣሚም የሰፋ ነው:: በተለይም ክረምት በመጣ ቁጥር ከፍተኛ የሆነ መቆራረጥ ይስተዋላል:: በዚህ ሳቢያ የከተማዋ ነዋሪ በከፍተኛ ደረጃ ቅሬታውን ሲያሰማ ይደመጣል::

እኛም ለዛሬው የተጠየቅ አምዳችን አገልግሎቱ በህብረተሰቡ የሚነሱ ኃይል መቆራረጥ ቅሬታዎች እና የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ማዕከል በማድረግ፤ አገልግሎቱ ችግሩን ከመፍታት አኳያ መሠረተ ልማቱ እንዲዘምን የማድረግ ሂደትን፤ ከሕዝብ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመቅረፍ የሄደበትን ርቀት፤ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በማንሳት የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ገበየሁ ሊካሳ (ዶ/ር) ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል::

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕዝብ ጥያቄንና ቅሬታን በሚመልስ መልኩ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅዳችሁ ምን ይዟል? ምን እየተሠራ ነው?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲታቀድ የ2015 በጀት አፈጻጸም የነበረውን ጉድለት ከመገምገም ይነሳል:: ስለሆነም በተለያዩ ባለድርሻ አካላት በመድረክ ተገምግመው ያሉ ድክመቶችን በማረም፣ በ2016 በጀት ዓመት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በሚያስችል መልኩ የታቀደ ነው::

በዚህ ረገድ ዕቅድ የሚጀምረው ከኮርፖሬት ሲሆን፤ ይሄም እስከ ታችኛው አገልግሎት መስጫ ድረስ የሚወርድ ነው:: በዚህም መሠረት ሀምሌ 01/2015 ላይ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ዕቅዶቻቸውን አውቀው ወደ ሥራ ገብተዋል። አተገባበሩም በየወሩ እየተገመገመ ሲሆን፤ ሂደቱም በተጨባጭም ለውጥ አምጥቷል። ለምሳሌ፣ ከግብዓት አቅርቦት አንጻር ሰፊ ዝግጅት ተደርጓል:: በመጀመሪያው ሩብ ዓመትም በአብዛኛው የዕቃ ግብዓትን በተገቢው ሁኔታ ማሟላት ተችሏል::

**አዲስ ዘመን፡- ካለፈው ዓመት ድክመት በመነሳት እየተሠሩ ያሉና ሊጠቀሱ የሚችሉ ምን ተጨባጭ ሥራዎች አሉ?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ባለፈው በጀት ዓመት እንደ ድክመት የተገመገመው ችግር መካከል አንዱ የኃይል መቆራረጥ ነው:: ለዚህ ደግሞ እንደ ምክንያት የተለየው የአየር ንብረት ነበር:: ከዚህ በተጓዳኝ ለኃይል ኔትወርክ መቆራረጥ ምክንያት ከሚሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ዛፎች ቀዳሚ ናቸው:: ለምሳሌ፣ ከሚቆራረጠው ኃይል ውስጥ 70 ከመቶው የሚሆነው ዋናው ኤሌክትሪክ ከመሬት ጋር ሲነካካ የሚከሰት ሲሆን፤ ይህን የሚያደርገው ባብዛኛው ዛፍ ነው::

ይሁን እንጂ ይሄን መቆራረጥ የሚያስከትሉ ዛፎችን ለመቁረጥ ያለው ፈተና ከባድ ነው:: ምክንያቱም፣ ዛፎች ይቆረጡ ሲባል ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጩኸት ይመጣል። ለምሳሌ፣ የከተማው አረንጓዴ ልማትና ውበት የሚባለው ተቋም 'ዛፎችን አልምቶ ለደረሱበት ደረጃ ብዙ ዘመን ፈጅቶብናል፣ መቁረጥ አትችሉም' ይላል:: እናም እስካሁን ለኃይል መቆራረጡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው አንዱ ጉዳይ ይህ ነው::

ስለዚህ በዚህ በጀት ዓመት ችግሩን ለማረም ከአረንጓዴና ከተማ ውበት ጋርና ከሌሎች የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር ምክክር እየተደረ ሲሆን፤ በተወሰኑ ጉዳዮች ስምምነት ላይ ተደርሷል:: በዚህም በየሳይቶች የሚከታተልና ትምህርት የሚሰጥ ባለሙያ ሰጥተው፣ አንዳንድ ቦታ ላይም ራሳቸው እንዲቆርጡ ውይይት እየተደረገ ነው:: በመሆኑም በመሠረታዊነት ለውጥ የሚመጣው ዛፎችን በመቁረጥ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል::

ይሄንን በመተግበር ረገድ፣ በመመሪያ ደረጃ በግራና በቀኝ በአምስት ሜትር ራዲየስ ውስጥ ዛፍ መኖር የለበትም። ይሄ ሲሆን የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቱ አይጎዳም:: ለምሳሌ፣ አሁን ላይ አጠቃላይ ወደ ሰባት ሺህ ኪሎ ሜትር በከተማ አስተዳደሩ የኤሌክትሪክ መስመሮች አሉ:: ከዚህ ውስጥ ሁለት ሺህ 200 ኪሎ ሜትሩ ከፍተኛ መስመር የሚባለው ነው:: በዛፎች እየተጎዳ ያለውም ይሄ ነው::

ከዚህ አኳያ ከባለድርሻ አከካላት ጋር ዛፎችን በተገቢው ቦታ እንዲተከሉና በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥሩ ለማስቻል የጋራ እቅድ እየታቀደ ነው:: ስለዚህ ከፍተኛ ለውጥ እናመጣለን። ሆኖም ሌላውና አሁንም ፈታኝ የሆነው ችግር ግን ዝናብና ከፍተኛ ነፋስ ነው:: ምክንያቱም ዝናብና ከፍተኛ ነፋስ ሲኖር የኃይል መቆራረጡ ይከሰታል።

**አዲስ ዘመን፡- ባለድርሻ አካላት የሚባሉት እነማን ናቸው? ምን የጋራ አሠራርስ አላችሁ?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ባለድርሻ አካላት የሚባሉት መንገዶች ባለሥልጣን፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልና የከተማ አስተዳደሩ ናቸው:: ችግሩን ከመገንዘብ እና በዘላቂነት እንዲፈታ ከማድረግ አኳያ ከሶስት ዙር በላይ በመከላከያና በከንቲባዋ ሰብሳቢነት በጋራ ታይቷል::

በዚህም አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ የሚጠበቅበት ከዛፍ ውጭ እንከን የሚፈጥሩ እንደ ወሰን ማስከበር ያሉ ሥራዎችን እንዲሠሩ ማድረግ ነው:: ምክንያቱም በከተማዋ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል የኔትወርክ ዝርጋታ በአብዛኛው ከመሬት በላይ ነው::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከመሬት በታች የሚዘረጉ ኬብሎች በዝተዋል። በእነዚህ ኬብሎች ላይም ቢሆን ጉዳት እየደረሰ ነው:: ይህም የሚሆነው በመሠረተ ልማት ገንቢ ተቋማት፤ በራሱ ጊዜና በተለያየ ምክንያት ሲሆን፤ ይህን ጉዳት ለመከላከል ተቋማት በትብብርና በቅንጅት የሚሠሩበት አግባብ ለመፍጠር እየተሠራ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ችግር ሲያጋጥም ብልሽቱን በቀላሉ ለይቶ መጠገን የሚያስችል ሁኔታ ፈጥራችኋል?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ብልሽት ሲጋጥም መለየት የሚያስችል መሣሪያ አለን:: ለምሳሌ፣ ከመሬት በታች ብለልሽት ማመልከቻ (underground fault locater) የሚባል አለ:: ይሄ መሣሪያ የቱ ጋር ብልሽት እንዳጋጠመ የሚጠቁም መሣሪያ አለ:: ከዚህ በፊት የነበረው መሠሳሪያ በቂ ስላልነበር ለመጠገን ፈተና ነበር። በመሆኑም አሁን ላይ በቂ መሣሪያ ስላለ ባለሙያዎች ተገቢውን ሥልጠና በመውሰድ ላይ ናቸው::

ለምሳሌ፣ በዚህ መሣሪያ ትክክለኛ ቦታቸው የተለዩ 45 የሚደርሱ ቦታዎች ላይ ብልሽት አጋጥሟል:: እነዚህ እስከ ጥር ድረስ ጥገና ይደረግላቸዋል:: ስለዚህ እነዚህን መሣሪያዎች በመጠቀም የኃይል መቆራረጡ ላይ የሚታይ ለውጥ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም የሆነው ከባለፈው በጀት ዓመት ድክመት በመነሳት ታቅዶ እየተሠራ ባለው ሥራ ነው:: በዚህ መልኩ በተከናወኑ ተግባራትም ብዙ የከተማዋ ክፍል ላይ የኃይል መቆራረጥ መሻሻል አሳይቷል::

**አዲስ ዘመን፡- የእናንተ አገልግሎት ከተማዋ የኃይል ፍላጎት አንጻር በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ፍላጎትና አቅርቦትን ከማጣጣም አኳያስ ምን ተሠርቷል?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** አቅርቦትና ፍላጎት ሲባል በዋናነት ከኃይል ማመንጫና ከተጠቃሚው ጋር ያለው ንጽጽር ነው። እንደ ሀገር የምናመነጨው አሁን ላይ አምስት ሺህ 300 ሜጋ ዋት ደርሷል:: ከሁለት ዓመት በኋላ ከህዳሴው ግድብ ጋር ተዳምሮ ወደ 11 ሺ ሜጋ ዋት ይደርሳል:: ያለው የኃይል ማመንጨት አቅም ትርፍ ነው:: ስለዚህ እንደ ኢትዮጵያ የሚጠቀመው ፒክ ሎድ ሁለት ነጥብ ሰባት ሜጋ ዋት አካባቢ ነው:: ስለዚህ ከፍላጎት አንጻር ሲታይ ያለው በቂ ነው:: ለዚህም ነው ለጎረቤት ሀገሮች መስጠት የተቻለው::

ከዚህ አኳያ ችግሩ የኔትወርኩ ሁኔታ ነው። ለምሳሌ፣ 10 ሺህ 500 የማሰራጫ ትራንስፎርመር አለ። እነዚህ ትራንስፎርመሮች አቅማቸው ሲሞላ ፊውዝ ይቃጠላል። የትራንስርመሮችን አቅም ለመቀየር የአቅርቦት ፈተናዎች ያጋጥማሉ:: በተመሳሳይ፣ ያረጁ ምሰሶዎች አሉ፤ እነዚህን ለመቀየር ጊዜና ገንዘብ ይፈልጋል::

አሁን ላይ ደግሞ በተለያየ ምክንያት ህብረተሰቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ጥገኛ ሆኗል:: ነገር ግን ኔትወርኩ በህብረተሰቡ ፍላጎት ልክ ዕድሳት ተደርጎለት አላለቀም። ያለው ፈተናም ይህ ነው:: እንደ አዲስ አበባም በአቅርቦቱና በተጠቃሚው ማህበረሰብ መካከል ያለው ልዩነት የተፈጠረው በሰብ ስቴሽን አቅም ምክንያት ነው።

ለአብነትም፣ በከተማዋ ስድስት የሚደርሱ ሰብስቴሽኖች አሉ:: ለምሳሌ፣ ኮዬ አቦ የሚባል ቦታ ያለው ሰብስቴሽን 500 ሜጋ ዋት አቅም አለው:: ስለዚህ ፈተናው ኔትወርኩን አሻሽሎ በቴክኖሎጂ አስደግፎ ለአገልግሎት ማብቃት ነው። ይህን ችግር ለማቃለልም ሥራዎች እየተሠሩ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ የኃይል አቅርቦት መቆራረጥ በህብረተሰቡ ዘንድ እየፈጠረ ያለው ምሬት ችግሩን አንገብጋቢ ከማድረጉ ጋር ተይይዞ እየተሠራ ያለው ተጨባጭ ሥራ ምንድን ነው?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** መንግሥት ለዘርፉ በስትራቴጅክ እቅዱ ትኩረት ሰጥቶታል:: ለምሳሌ፣ በኃይል ማመንጫ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው:: ይህም ምንጩ ከሌለ ቴክኖሎጂ ላይ ቢሠራ ትርጉም አልባ ስለሚሆን ነው:: በተመሳሳይ የኃይል ማስተላለፊያ ላይ ተሠርቷል። ከተሞች ውስጥ ያለው የኃይል ማሠራጫ ጣቢያ የተጀመረውም በቅርቡ ነው:: ምክንያቱም ኔትወርኩ ጥሩ ይዞታ ላይ አልነበረም።

ለምሳሌ፣ አዲስ አበባ ላይ ብቻ ሰባት ሺህ ኪሎ ሜትር የሚሆነውን መስመር ለማዘመን ተግዳሮቶች አሉ። ምክንያቱም እነዚህን ለመቀየር ፋይናንስ ማፈላለግ ይጠይቃል፤ ጊዜም ይፈልጋል:: የሚሠራው ከተማ ውስጥ እንደመሆኑም ሥራው አስቸጋሪ ነው:: በአንጻሩ፣ በገጠር አካባቢ አንድ የእንጨት ምሰሶን ወደ ኮንክሪት ለመቀየር ሌላ መንገድ ተይዞ ይሠራል::

ከተማ ላይ ግን ያንኑ እያጠፉን ነው የሚቀየረው። አንድ መስመር አምስት ጊዜ ይጠፋል:: ይህ ደግሞ ለመሠረተ ልማት ዝርጋታው ትልቅ ፈተና ነው። ምክንያቱም፣ የመብራት ዝርጋታ በየቦታው ፖል መትከልና ኔትወርክ መዘርጋትን ይጠይቃል:: የመብራት ቴክኖሎጂውም ቢሆን ምንም አይነት ሽግግር አላደረገም። ቀድሞም የሆነ ጀነሬሽንና ማስተላለፊያ መስመር ይኖራል፤ ፖል ይተከካል፤ ከዛም ህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል:: አሁን ላይም ያለው ይሄው ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ከማዘመንና በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ከማድረግ አኳያ ምን የታሰበ ነገር አለ?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማዘመንና ለማስተካከል በሁለት መልኩ እየተሠራ ነው። አንደኛው፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ምሰሶዎችን የማዘመን ሥራ ነው። ምክንያቱም የኔትወርኩ አጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ ያረጀ ነው:: እነዚህ ቢሆኑ መጀመሪያ የተዘረጉት ለትንሽ ደንበኛ ነው:: እናም ደንበኞች እየጨመሩ ሲመጡ አቅሙ ከፍ ማለት አለበት::

በተማዋ ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ የሕዝብ ቁጥር የሚጨምርበትና አገልግሎት ፈላጊው በየጊዜው እያደገ የመጣበት ሁኔታ አለ:: ይህንን ደግሞ ኔትወርኩ ማስተናገድ አይችልም:: ኔትወርኩ የተዘረጋው ደግሞ በእንጨት ምሰሶ በመሆኑ ከቆይታ በኋላ ያረጃል:: ከተማ ሲሰፋና ማስተር ፕላኑ ላይ የማስተካከያ ሥራ ሲሠራ አንዳንድ ኔትወርክ የማንሳት ሥራ ይሠራል:: ስለዚህ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አይደለም ለዚህም ነባራዊ ሁኔታው ደካማ ነው::

በመሆኑም ከ2010 በጀት ዓመት ወዲህ ስትራቴጂክ እቅድ ተቀርጾ የማሻሻያ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ሥራውም እየተሠራ ያለው በውጭ በተገኘ የፋይናንስ ምንጭ በመካከለኛ ቮልቴጅና በማሠራጫ ትራንስፎርመሮች ላይ ነው:: ይሄም «ኤሊቪ» የሚባል ወደ አራት ሺህ 700 ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ ከዚህ ወስጥ ሁለት ሺ ገደማ የሚሆነው መካከለኛ ቮልቴጅ ነው::

አንድ መካከለኛ ቮልቴጅ 50 ትራንስፎርመሮች ሊኖሩት ይችላል:: ይህ መካከለኛ ቮልቴጅ ተበላሸ ማለት 50 ትራንስፎርመር ኃይል ያጣል ማለት ነው:: ስለዚህ መጀመሪያ ትኩረት የተደረገው ሁለት ሺ 200 ኪሎ ሜትሩ መካከለኛ ቮልቴጅ ላይ ነው:: ከዚህ ውስጥ የአዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ማሻሻያ አደርጎ ለማጠናቀቅ የሚያስችል አራት ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ወደ ሥራ ተገብቷል::

**አዲስ ዘመን፡- አራቱ ፕሮጀክቶች የሚባሉት የተኞቹ ናቸው? በምን ያህል ገንዘብ ነው የሚከናወነው?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** የመጀመሪያው ስምንቱ ከተሞች

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## “በ2015 በጀት ዓመት 1213...

ከገጽ 6 የዞረ

የሚባሉት ናቸው፡፡ የፋይናንስ ምንጩ ዓለም ባንክና ኮፒክ የሚባሉ የፋይናንስ ተቋማት ናቸው፡፡ አዲስ አበባ ከስምንቱ ከተሞች አንዱ ነው፡፡ አብዛኛው አዲስ አበባ ውስጥ አለ። የክልል ዋና ከተሞች ላይ ከ2010 እስከ 2012 ተሰርቶ ተጠናቋል፡፡ በዚህም የክልል ከተሞች ከአዲስ አበባ የተሻለ የኔትወርክ ዝርጋታ አላቸው፡፡

ሁለተኛው፣ በቻይና ኤግዚን ባንክ ፋይናንስ የተደረገ ፕሮጀክት ነበር፡፡ በዚህም ሰባት መቶ ኪሎ ሜትር የሚሆን ኔትወርክ ዝርጋታ የመቀየር ሥራ ተሠርቷል። ሶስተኛው፣ በአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ ድጋፍ ሲሆን፤ በዚህም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ናቸው እየተገነቡ ያሉት። ይሄ ቴክኖሎጂ አንድ ኃይል ሲቋረጥ መቋረጡን ማመላከት የሚችልና ወዲያውኑ ጥገና መስጠት እንዲቻል የሚያደርግ ነው፡፡

አራተኛው ፕሮጀክት፣ በዓለም ባንክ ከተገኘ የፋይናንስ ምንጭ የሚሠራ ሲሆን፤ አሁን ላይ ኮንትራክተሮች ተለይተው ወደ ተግባር ገብቷል። ተግባሩም በ2017 መጨረሻ ላይ ይጠናቀቃል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የአዲስ አበባን መካከለኛ ቮልቴጅ ኔትወርክ በሙሉ ያሻሽላሉ፡፡ የአራት ሺህ የማሰራጫ ትራንስፎርመሮችን አቅም ያሻሽላል። በድምር ውጤቱም የአዲስ አበባን የኃይል መቆራረጥ በተጨባጭ ለውጥ ያሳያል፡፡

ይህ የሚሻሻለውም በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። አንዱ፣ አካላዊ ኔትወርኩን በማሻሻል ሲሆን፤ በዚህም ካሉት 10 ሺ 500 ትራንስፎርመሮች አራት ሺህ የሚሆኑት አቅማቸው ይሻሻላል፡፡ ይህ ሲሆን ጫናው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ኔትወርኩ በመሻሻሉና ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሰው ተጠቀመ አልተጠቀመ የሚቃጠል ፊውዝ አይኖርም፡፡ አሁን በከተማዋ የሚታየው የኃይል መቆራረጥ 60 በመቶ የሚሆነው በዕቅድ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ምክንያቱም ፖል ለመትከልና ኔትወርክ ለመዘርጋት ሙሉቀን ማቋረጥን ይጠይቃል። ስለዚህ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ በዕቅድ የሚቋረጥበት ሁኔታ አይኖርም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የእንጨት ፖሎችን በኮንክሪት ፖል የመቀር ሥራው ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ባለድርሻ አካላት ጋር ተግባብቶ ከመሥራት አኳያስ?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** በአንድ ከተማ የመሠረተ ልማቶች መቀናጀት ወሳኝ ነው፡፡ በተለይም አዲስ አበባ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በከተማ አስተዳደር ደረጃ የመሠረተ ልማት ቅንጅት የሚባል ተቋም ተቋቁሟል። ቅንጅቱ በምን ይገለጻል ቢባል በሚሠሩ መንገዶች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ ለዚህም የ‹‹ዩቲሊቲ›› መስመሮች በሙሉ ተዘርግተዋል፡፡ ስለዚህ መንገድ ሲሠራ የዩቲሊቲ መስመሮች ጋር ኤሌክትሪክ መስመር መቅበር ሲፈልግ ያለምንም ችግር ኬብል መቅበር ወይም መዘርጋት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በዚህ ጊዜ ያለው ኔትወርክ ምንም እንከን የለሽ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ፣የኢምፔሪያልና የለቡ ማሳለጫ መንገድ ሲሠራ በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቱ ላይ ከባድ ጉዳት ደርሷል፡፡ ይሄ የሆነው ከመሬት በታች የተቀበረ የኤሌክትሪክ መስመር ተዘርግቶ እያለ መንገድ የግድ መስፋት ስላለበት ይሄን በማድረግ ሂደት በተፈጠረ ጉዳት ነው፡፡ ይህ ቢቀናጅም ባይቀናጅም የሚቻል አይደለም፡፡

ምክንያቱም፣ ገመዱ መንገድ ማዕከል ውስጥ ይገባል። ይህን ለማስነሳት ጊዜ ይፈልጋል ብቻ ሳይሆን ኬብሉ በቀላሉ አይገኝም፡፡ ለመዘርጋት ኮሪደር መገኘት አለበት። አብዛኛው ጉዳት የሚደርስበት ግዴታ በሆነ የመሠረተ ልማት ሥራ በመኖሩ ነው፡፡ ለቡ ላይ ከዓመት በላይ የወሰደ ችግር ገጥሟል፡፡ ስለዚህ በመሠረተ ልማቱ ላይ ከግለሰብ ጀምሮ እስከ የመንግሥት ተቋማት ጉዳት ያደርሳሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በግለሰቦችም ሆነ በተቋማት በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ ጉዳት ሲደርስ ያለው ተጠያቂነት ምን ይመስላል?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ተያቂነት አለ፡፡ ለዚህም መደበኛ አካሄድና አሠራር አለው፡፡ ለደረሰው ውድመት ኬብሉን ከመተካት አንጻር ወጪውን ይሸፍናሉ፡፡ ነገር ግን ከተማው ላይ ብዙ ፈረሳና ግንባታዎች ስላሉ መቆጣጠር አይቻልም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የከተማዋ ነዋሪዎች ከአገልግሎት አሠጣጡና ከኃይል መቆራረጥ ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚያነሱትን ቅሬታ በተገቢው ጊዜ ምላሽ የመስጠቱ ሂደትን እንዴት ይገልጹታል?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ከኃይል መቆራረጥ ጋር የሚነሳው ቅሬታ ከአቅርቦትና ፍላጎት ጋር የሚያያዝ ነው። ባለፉት ዓመታት በተከናወነው ሥራ ከፍተኛ መሻሻል አለ፡፡ ነገር ግን በየጊዜው ከሚጨምረው የፍላጎት አቅም ጋር በቂ



አይደለም፡፡ በተለይ፣ የሠራተኞች በጎ ምላሽ አለመኖርና በቶሎው ደርሶ ጥገና አለማድረግ፤ ያልተገባ ጥቅም መፈልግ አለ፡፡ አገልግሎት አቅራቢ ሲኮን ደግሞ ለዚህ ተጋላጭነቱ ይኖራል፡፡

በመሆኑም ይህን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ በዚህም ተጨባጭ ውጤቶችም ተገኝተዋል። ለምሳሌ፣ በዚህ ላይ ክትትል ማድረግ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ከጂፒኤስ ጀምሮ አለ፡፡ በዚህም አዲስ ደንበኛ ከአመለከተበት ቀን ጀምሮ እስከሚገናኝበት ቀን ድረስ ያለውን ሂደት በማንኛውም ደረጃ፤ በትኛውም ቦታ ላይ ሆኖ መከታተል የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ኃይል ጠፋብኝ የሚል ቅሬታም ተመዝግቦ በጊዜው ጥገና ይደረጋል፡፡ ይህ በመሆኑ ሠራተኛው በጥንቃቄ ይሠራል።

ስለዚህ ርምጃ የሚወሰደው በጥርጣሬ ሳይሆን በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ ነው። ‘ኢንተርፕራይዝ ሪሶርስ ፕላኒንግ’ የሚባል አሠራር ተግባራዊ መደረጉም ችግሮች እንዲቃለሉ እያደረገ ነው። አሠራሩ ከተጀመረ ሶስት ዓመትን አስቆጥሯል፡፡ አንድ ትራንስፎርመር የት እንዳለ ይታወቃል፡፡ ይህ በመሆኑም የሠራተኛው ሥነምግባር ላይ ለውጥ አምጥቷል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አሠራሩ በመተግበሩ በተገልጋዩ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን መመለስ አስችሏል ለማለት ያስደፍራል?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ውጤታማ ነው ማለት አሁን ላይ ችግር የለም ማለት አይደለም፤ ችግሮች አሉ። 44 በመቶ የሚሆነው ሙስና አዳዲስ ደንበኞችን ከማስተናገድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስለዚህ ርምጃ የሚወሰድባቸው ከገማች እስከ ቆጣሪ ለጣፊ ድረስ ያሉ ሠራተኞች 44 ከመቶ የሚሆኑት ከአዲስ ደንበኛ ጋር የተገናኙ ናቸው። በሥነ ምግባር ማሻሻያ፤ በምክርና በሌሎች ክትትሎች መታረምና መመለስ ባልቻሉት ሠራተኞች ላይ ርምጃ ይወሰዳል፡፡

ለምሳሌ፣ በ2015 በጀት ዓመት 121 ሠራተኞች ላይ ከማስጠንቀቂያ እስከ ደሞዝ ማገድ የደረሰ አስተዳደራዊ ርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡ በቀጣይ ህብረተሰቡ ብልሹ አሠራሮችን ጥቆማ የሚሰጥበት ዌብሳይት እየበለጸገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በህብረተሰቡ ዘንድ የክፍያ አለመጣጣም፤ ለምሳሌ፣ በአንድ ወር መቶ ሃያ ብር የከፈለ ተጠቃሚ በሚቀጥለው ወር 30 ሺ ብር ቆጠረ ተብሎ ከአቅም በላይ የሚጠየቅበት ሁኔታ አለ፤ ይሄ ከምን የመነጨ ነው? ችግሩስ በምን መልኩ ይፈታል?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ይህ ከኔትወርኩ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ቆጣሪ አንባቢ ሜትሮቹ ከተተከሉ ቆይተዋል፤ ሁሉንም አያነቡም። ክትትል የሚደረግባቸውም በሰው ነው፡፡ ከሜትሮቹ የተረፈው የሚነበበው በሰው ነው። ሌላ ሀገር ግን ሲታይ ስማርት ሜትር ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ለመቀየር እየተሠራ ነው፡፡

በስድስት ወር አንድ ጊዜ የሚያነቡ አሉ፡፡ አንድ ጊዜ ሲያነቡ በደንብ ያነባሉ፤ እስከ ሚቀጥለው ስድስት ወር በግምት ይነበባል፡፡ አገልግሎቱ ሰው መክፈል ያለበት የተጠቀመበትን እንዲሆን በየወሩ ቆጣሪ ያነባል።

ችግር እንዳይፈጠር በኤም አር አይ እና በጂፒኤስ ሠራተኞችን እንከታተላለን፡፡ አልፎ አልፎ ቤት ይዘጋል። በዚህ ወቅት ቆጣሪ አንባቢ ገብቶ ማንበብ አይችልም። ይህ ሲሆን ትንሽ ብር ብቻ የሚወጣበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ሌላው ደግሞ ቆጣሪ አንባቢው ቤቱ ጋር ላይሄድ ይችላል፤ የተዘረጋው ሲስተም በብዛት የቀረፈ ቢሆንም ክትትሉ ሲበዛበት ቤቱ ድረስ ሄዶ ሳያነብ በግምት ይሞላል፡፡

አንዳድ ጊዜ ደግሞ የ‹‹ኢንኮዲንግ›› ስህተት ያጋጥማል፤ የተሳሳተ ቁጥር ሊሞላ ይችላል፡፡ ይህ ስህተት የሚጋጥማቸው ደንበኞች ከ2012 ጀምሮ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ አንባቢው ቦታው ድረስ ሄዶ ማንበቡ ማስረጃ በሲኤምአርአይ ይመጣል፡፡ ሰው አቅሙ በላይ ከቆጠረበትና መክፈል የማይችል ከሆነ እስከ ስድስት ወርና አንድ ዓመት ጊዜ ወስዶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

የተሳሳተ ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ ቅሬታ አቅርቦ እንዲታረም ይደረጋል፡፡ በከተማ አስተዳደሩ አንድ ሚሊዮን ቆጣሪዎች አሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ ግማሽ የሚሆነው የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ ደንበኛ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ባለፉት አራት ወራት የግብዓት አቅርቦት ላይ በትኩረት እንደተሠራ ገልጸዋል፤ በየትኞቹ አቅርቦቶች ላይ በምን ያህል በጀት ነው የተሠራው?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ግብዓቶቹ ኮንክሪት ምሰሶ፤ የእንጨት ምሰሶ፤ የኃይል ማሰራጫ ትራንስፎርመርና ኮንዳክተሮች፤ ሽቦ፤ ቆጣሪ፤ ኬብሎችና የመሳሰሉት ናቸው። ይህን ግብዓት ለማሟላት ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ግብዓት አቅርቦት ላይ ሰርተናል ስንል ባለፈው በጀት ዓመት ላይ ፈተናዎች ነበሩ፡፡ ፈተናዎቹን በመለየት በመሠራቱ ችግሮችን ቀድሞ በመለየት በተሠራው ሥራ ውጤት እየተመዘገበ ነው፡፡

በዚህም አንድ ሺህ 600 ኮንክሪት ምሰሶ ውል ተወስዶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የማሰራጫ ትራንስፎርመር እስካሁን የአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ከባዱ ፈተና ነበር፤ አሁን ላይ 291 ትራንስፎርመር ተገዝቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለኃይል መቆራረጥ 70 በመቶው ዛፎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፤ በዋናነት ከመልሶ ግንባታ ምሰሶዎችን ከመቀየርና ከዛፎች እንዲርቁ ከማድረግ አኳያ እስካሁን የተከናወኑ ሥራዎች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** ቅድም ዋና ዋና ፕሮጀክቶችን ገልጫለሁ፡፡ ዝቅተኛ መስመሩ አራት ሺህ 700 ኪሎ ሜትር በራስ አቅም ነው የሚሠራው፡፡ ለምሳሌ፣ ባለፈው በጀት ዓመት ሰሜን አዲስ አበባ ዲስትሪክት የሚባለውን አዲስ ክፍለ ከተማ ሙሉ በሙሉ ስድስት ሺህ የሚሆኑ የእንጨት ምሰሶዎችን ቀይሯል፡፡ የኮንክሪት ያልተደረገው ደግሞ በሲሚንቶ ዕጥረትና የዋጋ መናር ምክንያት ነው፡፡

የኮንክሪት ምሰሶ ዋጋ የእንጨት ምሰሶ ዋጋን አምስት እጥፍ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በኮንክሪት ብቻ ለማድረግ ብዙ ዓመታትን ይወስዳል፡፡ በዚህ ረገድ ፋይናንስ ትልቅ ፈተና ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የከተማው ማስተር ፕላን ኮንክሪት እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ ነገ የሚፈርስ ሰፈር ይኖራል፤ ስለዚህ በዛ ሰፈር የኮንክሪት ምሰሶን መዘርጋት እጥፍ ገንዘብ ይፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ጊዜ ከክፍያ ጋር ተያይዞ ደንበኞች “ባንክ ላይ ሲስተም የለም በመባሉ ምክንያት መብራት ያለምንም ማስጠንቀቂያ እንዲቋረጥብን እየተደረገ ነው፤” የሚል ቅሬታ ያሰማሉ፡፡ በዚህ ላይ የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነው?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** በጥቅምት ወር ባንክ ላይ በመሄድ የከፈሉ ደንበኞች 113 ሺህ 300፤ ሲቢኢ ብር በመጠቀም የከፈሉ 53፤ ቴሌ ብር በመጠቀም የከፈሉ 80 ሺህ፣ ሞባይል ባንኪንግ 161 ሺህ፣ ወደ ተቋሙ መጥተው የከፈሉ 12 ሺህ ሲሆኑ፤ በአጠቃላይ አራት መቶ 23 ሺ 947 ደንበኞች ከፍለዋል፡፡

ሆኖም ቴክኖሎጂ ሲሠራ የራሱ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ በባንክ አካባቢ ሲስተም አለመኖር ችግሮች አሉ፡፡ ነገር ግን መሰል ችግሮች በሁሉም ሳይሆን በውስን ደንበኞች ላይ የሚያጋጥም ነው፡፡ የአገልግቱ ሠራተኞች ሲስተም ስለሌለ ሳይሆን ይህ ደንበኛ አልከፈለም ብለው ነው የሚቆርጡት፡፡ ደንበኛው ባንክ ላይ ከፍሎም የሚቆረጥበት ሁኔታ አለ፡፡

ስለዚህ አንዳንድ ችግሮች ሲሰከቱ ለመፍታት አገልግሎቱ ቁርጠኛ ነው፡፡ እንደ አማራጭ ችግሩ ካጋጠመ መፍትሄ ለመስጠት የክፍያ ባለሙያዎች የካሽ ዴስክ አገልግሎት በየባንኩ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ሳይከፍል ሲቀር መቁረጥ፤ ሲከፍል መቀጠል ሥራ በጣም አሰልች ነው፡፡ ከዚህ አሠራር ለመውጣት ትኩረት እየተሠራ ነው። ይህን ለማስቀረት 600 ሺህ ቆጣሪ በዚህ በጀት ዓመት ወደ ስማርት ቆጣሪነት ይቀየራል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በኃይል መቆራረጥና መዋዠቅ ምክንያት የግለሰቦች መገልገያ የሆኑ እንደ ፍሪጅና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሣሪዎች ይቃጠላሉ፡፡ ለዚህ ጉዳት ምላሽ ከመስጠት አንጻር አገልግሎቱ ምን ያስቀመጠው አሠራር አለ?**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** በአጠቃላይ ይህንና መሰል ችግሮች የሚከሰቱበት ሁኔታ በጣም ውስን ነው፡፡ ኤሌክትሪክ የሚሠራበት ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎች አሉት። እያንዳንዱ መስመር የሚሠራው ዓለም አቀፍ ደረጃን መሠረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ ስለዚህ በብዛት አያጋጥምም።

ካጋጠመም የሚጎዳ ተሽከርካሪ ማሽኖችና ሞተር ላይ ነው፡፡ አውቶማቲክ ጀነሬሽን መቆጣራጠሪያ የሚባል አለ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሚፈጠረው አንዱ መስመር ተበጥሶ አንደኛው ኒውትራሉ ላይ ያርፋል፡፡ የሚያጋጥመውም በብዛት ሰፈር ላይ ነው፡፡ ስለሆነም መሰል ችግር ሲያጋጥም ማህበረሰቡ በ24 ሰዓት ውስጥ ሪፖርት ማድረግ አለበት። በዚህ መንገድ ልዩ ችግሮች ካልሆኑ ወደ እኔ መጥቶ አያውቅም፡፡ ደረሰኝ አገልግሎቱ ጠይቆ ያቀረበ ሲኖር የመተካት ሥራ ይሠራል፡፡

አንዳንዱ ከመሬት ተነስቶ አርባ ቴሌቪዥን ተቃጥሎብኛል ብሎ ሪፖርት የሚያቀርብ አለ። ይህ ትክክል አይደለም፡፡ ትክክለኛ መረጃ በመያዝ ለተቃጠለበት ንብረት ደረሰኝ ይዞ እንዲመጣ ይደረጋል። ስለሆነም በአሠራር መልስ የሚሰጥበት አግባብ አለ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**ዶክተር ገበየሁ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ሰማዩ ለብርቱዎች ብቻ ነው…

**ከገፅ 5 የዞረ**

ይናገራሉ፡፡

ሌተናል ጄኔራል ይልማ እንደሚሉት በ2010 ለውጡ ሲመጣ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በስም ብቻ የቆመ ባዶ ተቋም ሆኖ ነበር፡፡ በወቅቱ አንድም የማሠልጠኛ አውሮፕላን አልነበረም። ለወታደራዊ አገልግሎት የሚውል አንድም ሂሌኮፕተር አልነበረም። በዚህ የተነሳ ተቋሙ ወረራ ቢገጥመው አንዳችም ለመከላከል የሚያስችል ቁመና ላይ አልነበረም፡፡

በ2001 እንደተመረቁ የሚናገሩት የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊው ሻለቃ ካፒቴን ሰይድ በበኩላቸው፤ እሳቸው በሚማሩበት ወቅት ከዩኒቨርሲቲ ተመልምለው ወደበረራ ትምህርት ቤት ሲመጡ በቂ አውሮፕላን ባለመኖሩ ለብዙ ጊዜ ልምምድ ሳያደርጉ መቆየታቸውን ፤ በዚህ የተነሳ ተስፋ ቆርጠው እንደነበርም ይገልጻሉ፡፡ በወቅቱ ተመልምሎ የመጣ ተማሪ ምንም ሥልጠና ሳይወስድ ቀጣይ ዙር ሠልጣኝ ይመጣ እንደነበርም በቁጭት ተናግረዋል፡፡

## ሪፎርምና አየር ኃይል

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከሪፎርም በፊት የነበረበት ቁመና ከላይ እንደተገለጸው በርካታ ችግሮች የነበሩበት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ አውሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች የበረራ ጊዜያቸው በመጠናቀቁ ቆመዋል፡፡ የሥልጠና አውሮፕላንም ባለመኖሩ ሥልጠና ለመስጠት የሚቻልበት ቁመና ላይ አልነበረም፡፡ ከዚያ በተጨማሪ ትላልቆቹ አንቶኖቭ አውሮፕላኖች እና ሚግ 23 የመሳሰሉ ተዋጊ አውሮፕላኖች ለብዙ ጊዜ በመቆማቸው ለሥራ ዝግጁ የሆነ አውሮፕላን አለ ለማለት የማይቻልበት ሁኔታ ነበር፡፡

ነገር ግን በሪፎርም የተወሰደው የመጀመርያው ርምጃ አስፈላጊ የሆኑ የመለማመጃ አውሮፕላኖችን መግዛትና ጥገና የሚስፈልጋቸው አውሮፕላኖች እንዲጠገኑ ማድረግ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ታዲያ በተለይ ከጥገናው ጋር በተያያዘ ሌላ ፈተና ከፊት ተደቀነ፡፡ ይህም አብዛኞቹ አውሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች የበረራ ሰዓታቸው በመጠናቀቁ ዳግም ወደሥራ ለማስገባት ተጭነው ወደተሠሩበት ኩባንያ መውሰድ የግድ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በወቅቱ መንግሥት ከነበረበት የፋይናንስ ችግር አንጻር የሚታሰብ አልነበረም፡፡ እናም መላ ማፈላለግ ተጀመረ፡፡

በዚህም መሠረት አውሮፕላኞቹን እና ሄሊኮፕተሮቹን ከተሠሩባቸው ኩባንያዎችና መንግሥታቸው ጋር በመነጋገር ባለሙያዎች እዚህ መጥው ጥገና እንዲያደርጉ በማግባባት ብዙዎቹን አውሮፕላኖች እና ሄሊኮፕተሮች ወደሥራ ለመመለስ ተችሏል፡፡ በወቅቱ አውሮፕላኖቹንና ሄሊኮፕተሮቹን ወደሥራ ከመመለስም ባሻገር ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የተገኘው የእውቀት ሽግግር ለተቋሙ ትልቅ እድል የሰጠ ነበር፡፡

ተቋሙ በዚህ መልኩ ራሱን በመጠኑም ቢሆን እንዲያገግም ካደረገ በኋላ በመንግስት ቁርጠኛ ድጋፍ እና በባለሙያዎችና አመራሮች የሌት ተቀን ጥረት በየጊዜው ራሱን እያሳደገና እየተሻሻለ ዛሬ ከሀገር አልፎ ለአፍሪካ ተምሳሌት መሆን የሚችል ተቋም ሊሆን በቅቷል፡፡

## የተቋሙ የጥገና አቅም

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አየር ኃይል የጥገና ማዕከል እጅግ ከፍተኛ አቅም መፍጠር ችሏል። በማዕከሉ ማንኛውም አይነት እውሮፕላን ይጠገናል፤ ይህ ብቻ አይደለም፤ አውሮፕላኖች የበረራ ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ወደውጭ ተጭነው በመሄድ ሲደረግ የነበረው ዳግም ወደሥራ የመመለስ ሥራ አሁን እዚሁ ማከናወን የሚችሉ ባለሙያዎችን መፍጠር ተችሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ቀደም ሲል ማንዋል

> **በርግጥ ስለዚህ ተቋም በዚህ አጭር ጽሁፍ ቀርቶ መጽሀፍም ቢጻፍ በልኩ ማስረዳት ይቻላል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ምክንያቱም ተቋሙ የተገነባበት መንገድ ዘርፈ ብዙ ነው። ሆኖም ግን በጥቂቱ እንካችሁ**

የነበሩ እውሮፕላኖች ዲጂታል እንዲሆኑ በማድረግ አቅማቸውን የማሳደግ ሥራም በዚሁ ማዕከል የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ በአጠቃላይ ማዕከሉ ያለምንም ችግር ማንኛውንም አውሮፕላን ከቅድመ በረራ ጀምሮ እስከ ድህረ በረራ ጥገናና ክትትል እንዲሁም ቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎችን በብቃት የመከወን አቅም ላይ ደርሷል፡፡

## የሥልጠና አቅም

የአየር ኃይል የሥልጠና ማዕከል ቀደም ሲል በርካታ ችግሮች የነበሩበት ነው፡፡ ቴክኒሺያኖችም ሆኑ የበረራ ባለሙያዎች በቂ ግብዓት ባለመኖሩ ትምህርታቸውን ለመከታተል ከፍተኛ ችግር ነበረባቸው፡፡ ከወጡ በኋላም ቢሆን በየጊዜው ራሳቸውን ለማሻሻል የሚያስችል አቅም ባለመኖሩ አብራሪዎች ከሀገር የሚጠፉበት አጋጣሚዎችም የተፈጠሩባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት የበረራ ማዕከሉ ራሱን በልዩ ልዩ ቁሳቁስ ከማደራጀቱም በላይ የካሪኩለም/የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ ጭምር በማድረግ ትልቅ ተቋም መሆን ችሏል፡፡ በዚህም በአሁኑ ወቅት ከራሱ አልፎ ከበርካታ የአፍሪካ ሀገራት የሥልጠና ጥያቄዎች የሚቀርብለት ተቋም ነው፡፡

ተቋሙ ባለሙያዎችን ሲያሰለጥንም ነገን ታሳቢ በማድረግ ከቴክኒክ ሙያው በተጨማሪ ተጨማሪ የአመራር ትምህርት ይሰጣል። ይህም ባለሙያዎቹ ለቀጣይ መሪ መሆን የሚያስችላቸውን ክህሎት እንዲያገኙ የሚረዳ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተቋሙ ውስጥ ሠልጣኙና በመደበኛ ሥራ ላይ ያለው ባለሙያ አለባበስም ተመሳሳይ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የሠልጣኞች የራሳቸው የአለባበስ ሥርዓት እንዲኖራቸው በማድረግ ዲሲፕሊን አንዱ መርህ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ዲሲፕሊን የአየር ኃይል አንዱ መገለጫ ነው። እያንዳንዱ ሠራተኛም ሆነ ተማሪ በጊቢው ውስጥ ሲንቀሳቀስም ሆነ ሲሠራ ወታደራዊ ዲሲፕሊንን በጠበቀ መልኩ ነው፡፡ “discipline is a Soule of a soldier ” የሚለው መርህም በጊቢው ውስጥ ጎልቶ ይስተዋላል፡፡

የሥልጠና ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት በኮምፒውተር የታገዘ፣ በቂ የማስተማሪያ ግብዓት የተሟሉለት እና ምቹ የመማርያ ሥፍራ የተመቻቸለት ዘመናዊ ተቋም ሆኗል። ለምሳሌ በማዕከሉ በረራ የሚለማዱባቸው በቂ አውሮፕላኖች፣ ለበረራ ቅድመ ዝግጅት የሚረዱ “የሲሙሌተር” ምስለ በረራ ማካሄጃ መሳሪያዎች፣ ልዩ ልዩ የአውሮፕላን ክፍሎች፣ ዲጂታል መሣሪያዎች ወዘተ የተሟላ ነው፡፡

## ምቹ የሥራ አካባቢን የመፍጠር ሥራ

ተቋሙ ከሪፎርሙ በኋላ በትኩረት ካከናወናቸው ተግባራት አንዱ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን የማሟላት ሥራ ነው፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ሁኔታ በጊቢው ውስጥ ያለው የመብራት አገልግሎት የሚቆራረጥ፣ በቂ ውሃ ያልነበረው፤ የኢንትርኔት አገልግሎቱም የማያስተማምን ነበር። በዚህ የተነሳ ተቋሙ ዓለም ከደረሰበት የዘርፉ ቴክኖሎጂ አንጻር ብዙ ክፍተቶች ነበሩበት፡፡

በዚህም የተነሳ ከሪፎር በኋላ አንዱ ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ ያከናወነው አስተማማኝ የመሠረተ ልማት ፍላጎት እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡ በዚህ መሠረት በጊቢው ውስጥ ታዳሽ ኃይልን በመጠቀም አስተማማኝ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ተገንብቷል፤ የኔትወርክና የውሃ መሠረተ ልማቶችን እንደገና በመገንባት አስተማማኝ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ለስራው በቀጥታ አስፈላጊ በመሆኑ ተቋሙ ለሚወስዳቸው ማናቸውም ተልዕኮዎች ምቹ ሆኔታ እንዲኖር የሚያደርጉ ናቸው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ተቋሙ ጊቢውን ለእይታ ማራኪ ለማድረግ የሄደበት ርቀት ተቋሙን የሚሠሩበት ብቻ ሳይሆን ዘና እያሉ የሚሠሩበት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በጊቢው ውስጥ የተተከሉት ዛፎችና ልዩ ልዩ አትክልቶች፣ አረንጓዴ ሥፍራዎች፣ መንገዶችና መዝናኛ ሥፍራዎች ለመኖርያነት ታስበው የተገነቡ በመሆናቸው ለሠራተኛው ደስተኛ ሆኖ እንዲሠራ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ካረፈበት ሰፊ ስፍራ አንጻር፤ ለዘመናት ያለ ሥራ የቆየ መሬትን በማልማት ባለፈው ዓመት ከስምንት መቶ ኩንታል በላይ ስንዴ በማምረት ጠጨማሪ የገቢ ምንጭ መፍጠር ተችሏል።

## በዓሉ ለምን ይከበራል

ሌተናል ጄኔራል ይልማ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በዓሉን ሲያከበር አራት ዋና ዋና ቁልፍ ሥራዎችን ታሳቢ ያደርጋል፡፡ እነዚህም የሰው ኃይል ልማት፣ ትጥቅ፣ መሠረተ ልማት እና ኢትዮጵያን የሚመጥን አየር ኃይል የመገንባት ተልዕኮ ናቸው፡፡

የሰው ኃይል ልማት የተቋሙ የሪፎርም ዋነኛ ተግባር ነው፡፡ በተለይ ብቁና ሥነምግባርን የተላበሰ ባለሙያን ማፍራት የተቋሙ ዋነኛ ተልዕኮ ነው። ከዚህ መነሻነት ተቋሙ በሥልጠና ማዕከሉ አማካኝነት ብቃት ያላቸው የበረራ ባለሙያዎችን፣ ቴክኒሺያኖችና ሌሎች ባለሙያዎችንም በማሠልጠን ለሥራ ዝግጁ እያደረገ ነው፡፡

ለዚህም ተቋሙ ቀደም ሲል ሲሰጥ የነበረውን ካሪኩለም/ሥርዓተ ትምህርት ጭምር በማሻሻል እና ለነገ ተቋሙን ተረክበው ሊመሩ የሚችሉ ባለሙያዎች የተሟላ እውቀትና ክህሎት የሚያገኙበት እንዲሆን እያደረገ ይገኛል፡፡

ከትጥቅ አንጻርም ተቋሙ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ አሉ የሚባሉ የውጊያና የሥልጠና ትጥቆችን አሟልቶ የያዘ ተቋም ሆኗል፡፡ መሣሪያዎቹም ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ የተደራጁ ናቸው፡፡

ከመሠረተ ልማት አንጻር ለሥራና ለሠራተኛው ምቹ የሥራ አካባቢን ለመፍጠር በተሠራው ሥራ ተቋሙ በርካታ መሠረተ ልማቶች ገንብተዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በ44 ወራት ጊዜ ውስጥ የተገነባው ስታዲየም፤ ደረጃውን የጠበቀና ለተቋሙ መኮንኖች ብቻ ሳይሆን ለከተማዋ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚሰጠው የመኮንኖች መዝናኛ ክበብ እንዲሁም የጊቢውን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ዘመናዊ ካሜራዎች ለተቋሙ እድገት የራሳቸውን አወንታዊ ሚና እየተጫወቱ ነው፡፡

በዚህ በዓል ከ26 የአፍሪካ ሀገራት አየር ኃይል የሚመጡ እግዶች የሚገኙ ሲሆን ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ሃላፊዎችና መሪዎች እንዲሁም የወዳጅ ሀገራት እንግዶች እንደሚገኙ ይጠበቃል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የውጭ ሀገራት እንግዶች እና የሀገር ውስጥ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ሃላፊዎች የሚሳተፉባቸው የፓናል ውይይቶች የሚከናወኑ ሲሆን፤ በመጨረሻም የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከወዳጅ ሀገራት አየር ኃይሎች ጋር በመሆን የሚያሳዩት የአየር ላይ ትርኢት በአይነቱ ልዩ ሆኖ የሚከበር ይሆናል። በመዝጊያ ሥነሥርዓቱ ላይም ልዩ ልዩ ባለሙያዎች ይመረቃሉ፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የመጣባቸው ወጣ ገባ መንገዶች እና አሁን የደረሰበት ደረጃ ሲታይ ትልቅ ትምህርት የሚቀሰምበት ነው፡፡ በተለይ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በበዓሉ ላይ መታደማቸው ተቋሙ የደረሰበትን ደረጃ ለማሳየትና በዘርፉ ለሌሎችም ተሞክሮውን የሚያካፍልና ተያይዞ ለማደግና ከራስም አልፎ ለሌሎች መከታ ለመሆን የሚያስችለውን አቅም የገነባ ተቋም መሆኑን ለማሳየት ትልቅ እድል የሚሰጥ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተቋሙ የሕዝብ ሀብት የፈሰሰበት እና ከሕዝቡ የወጡ ልጆች የሚያንቀሳቅሱት ተቋም እንደመሆኑ ስለተቋሙ አጠቃላይ ሁኔታ ለሕዝብ ማሳየት አስፈላጊ ነው፡፡ ሕዝብም ስለራሱ ተቋም የማወቅ መብት እንዳለው ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ይህ በዓል ይህንን ታሳቢ በማድረግ አጠቃላይ ስለተቋሙ መረጃ ለመስጠት የተሻለ አጋጣሚ የሚፈጥር ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተቋሙ አሁን ከደረሰበት ደረጃ አንጻር ሲታይ ለነገው ትውልድ ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡ ስለዚህ ወጣቱ ትውልድ ይህን ተቋም ለመቀላቀል ትልቅ ፍላጎት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ስለተቋሙ ነባራዊ ሁኔታ በቂ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በዓሉ እነዚህን እና መሰል ጥያቄዎችን በመመለስ ስለተቋሙ አስፈላጊ መረጃዎችን እንድናገኝ የሚያስችል በመሆኑ የበዓሉ መከበር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የጎላ ነው፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በአንድ ቀን ጉብኝት ብቻ የሚታወቅና ሊነገርለት የሚገባው ተቋም አይደለም፡፡ ስለተቋሙ እያንዳንዱን ነገር ለመጎብኘት ቀናት አልያም ሳምንታትን ሊወስድ ይችላል፡፡ ነገር ግን እኛ በአንድ ቀን ቆይታችን እጅግ በጣም ጥቂቱን ብቻ ነው ማየት የቻልነው። ወደፊት ስለተቋሙ ለማወቅ ፍላጎቱ ያላቸው ሰዎችም ሆኑ ባለሙያዎች ግን ብዙ የሚነገር ታሪክ አየር ኃይል ውስጥ እንዳለ ሊገነዘቡ ይገባል እላለሁ፡፡

ቸር እንሰንብት !

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## ስግብርናው ዘርፍ ቴክኖሎጂን ያስተዋወቀ የንግድ ትርኢት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በሀገሪቱ በርካታ አውደ ርዕይና ባዛሮች //የንግድ ትርኢቶች/ እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ በተለያዩ የግልና የመንግሥት ተቋማት አዘጋጅነት የሚሰናዱ መርሀ ግብሮች የንግዱን ማህበረሰብንና አርሶ አደሮችን ከሸማቹ ጋር በቀጥታ በማገናኘት ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመንባቸዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲዘጋጁ ደግሞ የሀገሪቱ ኩባንያዎች፣ አቅራቢዎች እና ላኪዎችን ከዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በር ከፋች ይሆናሉ። የንግድ ትርኢቶች በዋናነት የገበያ ትስስርን በመፍጠር፣ የልምድ ልውውጥ በማድረግና በሀገር ውስጥ ያለውን የቴክኖሎጂና የምርት አቅም ለመረዳት የሚያግዙ ናቸው።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶችን ማካሄድ ጉልህ አበርክቶ እንዳለው ይታሰባል፡፡ ምክንያቱም ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን ከማስተዋወቅና የገበያ ትስስር ከመፍጠር ባለፈ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የልምድ ልውውጥ ማድረግ የሚችሉበትን ሰፊ ዕድል መፍጠር ስለሚያስችል ነው። በተለያየ ጊዜ የተካሄዱ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን እንዳስገኙላቸው ተሳታፊዎች ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

ከሰሞኑም በአምራች ኢንዱስትሪዎችና በንግዱ ማህበረሰብ መካከል ትስስር ይፈጥራል፤ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ያመላክታል የተባለለት 14ኛው ዓለም አቀፍ የእርሻ እና የምግብ ንግድ ትርዒት ከሰሞኑ ተካሂዷል፡፡ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት ለሦስት ተከታታይ ቀናት የተካሄደ ሲሆን፤ የተለያዩ አምራቾች እና ኢንዱስትሪዎች ተሳታፊ ሆነውበታል፡፡

አምራቹን ከሸማቹ እንዲሁም ግብዓት አቅራቢውን ከኢንዱስትሪዎች ጋር የሚያገናኘው ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች የገበያ ትስስር በመፍጠር፣ የቴክኖሎጂና የልምድ ልውውጥን ለማቀላጠፍ የጎላ አበርክቶ እንዳላቸው በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ የተሳተፉ አምራቾች፣ የግብርና ግብዓት አቅራቢዎችና ኢንዱስትሪዎች ይናገራሉ፡፡

በንግድ ትርዒቱ ከተሳተፉት አምራቾች መካከል የማሸጊያ ምርቶችን ይዞ የቀረበው ክላሲክ ፓኬጂንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት አንዱ ነው፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራት የድርጅቱ የገበያ ልማት ባለሙያ ወይዘሪት ፋንቱ ደገፉ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ የገበያ ትስስር ለመፍጠርና እርስ በእርስ ለመተዋወቅና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ገልጻለች። በዚህ ረገድ ውጤታማ ተሞክሮ ማግኘታቸውንም ትገልፃለች።

እሷ እንዳለችው፤ ክላሲክ ፓኬጂንግ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ማሸጊያዎችን ያመርታል፡፡ ለአብነትም ለምግብ፣ ለጨርቃ ጨርቅ፣ ለኮንስትራክሽን፣ ለወተትና ለሌሎችም አገልግሎት የሚውሉ ማሸጊያ ምርቶችን ያመርታል፡፡ መድረኩም እነዚህን ምርቶች ከሚፈልጉ አምራቾች ጋር በመተዋወቅ የገበያ ትስስር መፍጠር ያስችላል፡፡ ከዚህ ባለፈም ግብዓት አቅራቢ ከሆኑ ድርጅቶች ጋርም እንዲሁ የመተዋወቅ ዕድል በመፍጠር ለማሸጊያ ምርቶቹ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን የማግኘት ዕድል ፈጥሯል፡፡

የማሸጊያ ምርቶቹ ለምግብና ምግብ ነክ ላልሆኑ ምርቶች አገልግሎት የሚውሉ በመሆናቸው ድርጅቱ ማሸጊያዎቹን በሀገር ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ አምራች ድርጅቶች ያቀርባል፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ አምራች ድርጅቶች በተጨማሪ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ጭምር ምርቶቹን ተደራሽ ያደርጋል፡፡

በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱም ድርጅቱን ማስተዋወቅ መቻሉን የጠቀሰችው ወይዘሪት ፋንቱ፤ ደንበኞችን ማግኘትና ፕላስቲክ ማሸጊያዎቹን ከሚፈልጉ አምራች ድርጅቶች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር መቻሉንም ነው ያስረዳችው፡፡ ከግብዓት አቅራቢዎች ጋርም እንዲሁ የመተዋወቅ ዕድል መፍጠሩን በመጥቀስ የንግድ ትርዒቱን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አመልክታለች፡፡

በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ተሳታፊ በመሆን የተለያዩ ጠቀሜታዎችን አግኝቻለሁ የሚለው ሌላኛው ተሳታፊ ያሳርት ኢንጅነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ ላለፉት 18 ዓመታት በኤሌክትሮ ሜካኒካል ቢዝነስ ውስጥ የቆየና በዘርፉ በጎ ተጽዕኖ እየፈጠረ ስለመሆኑ የድርጅቱ የጨረታና ማርኬቲንግ ባለሙያ ወጣት ናዝራዊት አርዓያ ትናገራለች፡፡

ወጣት ናዝራዊት እንዳለችው፤ ድርጅቱ በንግድ ትርኢቱ የተለያዩ ምርቶችን ይዞ ቀርቧል፤ በተለይም በግብርና ግብዓቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራቱና ከአርሶ አደሩ ጋር ቅርበት ያለው ድርጅት በመሆኑ በተለይም የግብርና ሥራዎችን ቀልጣፋና ምቹ ሊያደርጉ የሚችሉ ግብዓቶችን ያስመጣል፡፡ ለአብነትም የጠብታ መስኖ፣ የቡና መፈልፈያና መገልፈፊያ እንዲሁም ማቀነባበሪያ ማሽኖችን ለአርሶ አደሩ እያቀረበ ይገኛል፡፡

ድርጅቱ አርሶ አደሩን ለማገዝና የግብርና ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩትና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመሆን ይሠራል፡፡ በእስካሁኑ የሥራ እንቅስቃሴውም ኢትዮጵያ ውስጥ 160 በሚደርሱ አካባቢዎች የግብርና ግብዓቶችን በማቅረብ ተደራሽ ማድረግ ችሏል፡፡

ከሚያቀርባቸው ቴክኖሎጂዎች መካከልም በሶላር የሚሰሩ ፓምፖች ይገኙበታል፤ ፓምፖቹ ገጠራማ በሆኑ አካባቢዎች ሥራ ላይ ቢውሉ አርሶ አደሩ ከወንዝና ከተለያዩ የውሃ አካላት ውሃ እየጠለፈ በመስኖ እንዲያለማ ማድረግ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ድርጅቱ የግብርና መሣሪያዎችንና ማሽነሪዎችን በሀገር ውስጥ ገጣጥሞ የሚያቀርብ ሲሆን፣ ለዚህም ዋና ዋና የተባሉ ግብዓቶችን ከውጭ በማስገባት እንደሚሠራ ነው ወጣት ናዝራዊት የገለጸችው፡፡

እሷ እንዳለችው፤ ከውጭ ዋና ዋና ግብዓቶችን በማስመጣት በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ የተለያዩ የእርሻ መሣሪያዎች አሉ፡፡ እነዚህን የእርሻ መሣሪያዎች በማምረት በአራቱም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ምርቶቹን ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡ በተለይም ለአርሶ አደሩ የቡና ማሽን፣ የወተት እንዲሁም የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያና ሌሎችንም በማቅረብ ምርትና ምርታማነታቸው እንዲጨምር የማድረግ ሥራን በስፋት ይሠራል፡፡

እንዲህ ያሉ መድረኮች ድርጅቱን በማስተዋወቅና የገበያ ትስስር በመፍጠር ረገድ ትልቅ አቅም መፍጠር እንደሚያስችሉ የጠቀሰችው ወጣት ናዝራዊት፤ በተለይም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እየተመሩ የሚመጡ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮችን የመተዋወቅ ዕድል ሰፊ እንደሆነ ጠቅሳለች፡፡ ይህም ሰፊ የሆነ የገበያ ትስስር እንደሚፈጥርና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋርም እንዲሁ ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር እንደሚያስተሳስር አስረድታለች፡፡

ዋና ዓላማውን በገበያ ማረጋጋት ላይ አድርጎ የሚሠራው የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ከተሳተፉ ድርጅቶች መካከል ነው፡፡ ወይዘሮ ስንታየሁ እንዳለ የኮርፖሬሽኑ የምርት ጥራት ባለሙያ ናት፡፡ እሷ እንደተናገረችው፤ የምርት ጥራት ባለሙያዋ ኮርፖሬሽኑ አራት ዘርፎችን አዋቅሮ የያዘ ሲሆን፣ እነሱም አለ በጅምላ፣ ኢትፍሩት፣ እህልና ቡና እንዲሁም ግዢ ማማከር ናቸው፡፡ ኮርፖሬሽኑ ገበያ የማረጋጋት ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል። በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱም የተለያዩ ምርቶችን ይዞ ቀርቧል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የምግብ ሸቀጦችን ለሸማቹ የሚያቀርበው በተመጣጣኝ ዋጋ ነው፡፡ በተለይም ስኳር፣ ዘይት፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ጤፍን ጨምሮ በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጤፍ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ የጨመረበት ሁኔታ መፈጠሩን ወይዘሮ ስንታየሁ በመጥቀስ፤ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ኮርፖሬሽኑ ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በቅንጅት በመሥራት ምርቶቹን በቀጥታ በመግዛት ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ሲያቀርብ ቆይቷል፤ አሁንም እያቀረበ ይገኛል ብላለች፡፡ በዚህም ገበያውን ማረጋጋት መቻሉን ጠቅሳ፣ ለአብነትም ጤፍ ለተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በማቅረብ ለሠራተኛው መፍትሔ መሆን ችሏል ብላለች፡፡

ወይዘሮ ስንታየሁ ዓለም አቀፍ የእርሻ እና የምግብ ንግድ ትርዒቱ ፈላጊና ተፈላጊን በማገናኘት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጻለች፡፡ ኮርፖሬሽኑ ሸማቹን የሚያገኝበት ምንም አይነት መድረክ ባለመኖሩ አብዛኛው ሸማች ኮርፖሬሽኑ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች አያውቅም፡፡ ስለዚህ እንዲህ ያሉ መድረኮች ሸማቹን ከአምራቹና ከአቅራቢዎች ጋር በማገናኘት እንዲሁም ግብዓት አቅራቢዎችን ከኢንዱስትረዎች ጋር በማስተሳሰር ጉልህ አበርክቶ እንዳላቸው ገልጻለች፡፡

በንግድ ትርዒቱ ዓለም አቀፍ አምራች ኩባንያዎች መሳተፋቸው ሌላው ዓለም በቴክኖሎጂና በእውቀት የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ ዕድል የፈጠረ እንደሆነና የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎችና አርሶ አደሮች ምርቶቻቸውን በላቀ ደረጃ ማምረት የሚችሉበትን የልምድ ልውውጥ ማግኘት የቻሉበት መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የንግድ ትርኢቱ በተለይም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተጀመሩ የሌማት ትሩፋት ፕሮጀክቶች ውጤታማነትም የላቀ አበርክቶ እንዳለው የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የንግድና ግብይት ዘርፍ ምክትል የቢሮ ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ ተናግረዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ የከተማ ግብርናን ለማስፋፋት በከተማ አስተዳደሩ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን ይበልጥ በማጠናከር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተደረገ ላለው ጥረት ስኬትም በጎ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው ስለ ንግድ ትርኢቱ ሲናገሩ እንደሚገልፁት፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ግብርና ላይ የተመረኮዘ እንደመሆኑ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ በተለይም በግብርናው መስክ የተሠማራውን የግሉን ዘርፍ ለማጠናከር ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች ግብርናውን በማዘመንና የግብርና ውጤቶችን ምርታማነት በመጨመር ሀገሪቱ በዘርፉ ያላትን አቅም ማሳደግና ከዘርፉም መጠቀም እንድትችል ሰፊ ሥራ መሥራት ይገባል።

የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው መስክ ያለውን አነስተኛ ሚና መጨመርና ግብርናውን በኢንዱስትሪ ማላቅ እንደሚገባ ያመለከቱት ፕሬዚዳንቷ፤ የተቀመጠውን ግብ ለመምታት እዚህም መሰል ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እዳላቸው አመላክተዋል። በተለይም በአምራቾች፣ በኢንዱስትሪዎችና በንግዱ ማኅበረሰብ መካከል ትስስር ለመፍጠርና ለዓለም አቀፍ አምራቾች የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማመላከት ረገድ የሚኖረው አስተዋጽኦ ሰፊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በ14ኛው ዓለም አቀፍ የእርሻ እና የምግብ ንግድ ትርዒት ከኬንያ፣ ሞሮኮ፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች፣ ቱርክ፣ ኮሶቮ፣ ሞሪሺየስ እና ሕንድ የመጡ ኩባንያዎችን ጨምሮ በርካታ የሀገር ውስጥ አርሶ አደሮችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ተሳትፈውበታል። የከተማ አስተዳደሩ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ የግብርና ፕሮጀክቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ገልጿል። መሰል ዝግጅቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ኩባንያዎች መካከል የንግድ ትስስር ለመፍጠርና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን አዘጋጆቹና ተሳታፊዎቹ ሲናገሩ ተደምጠዋል።



የንግድ ትርኢቱ በተከፈተበት ወቅት

**በዚህ በ14ኛው ዓለም አቀፍ የእርሻ እና የምግብ ንግድ ትርዒት ከኬንያ፣ ሞሮኮ፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች፣ ቱርክ፣ ኮሶቮ፣ ሞሪሺየስ እና ሕንድ የመጡ ኩባንያዎችን ጨምሮ በርካታ የሀገር ውስጥ አርሶ አደሮችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ተሳትፈውበታል**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሥልጣኔ እና ሰብዓዊ መብት

**ዋለልኝ አየለ**

ሰሞኑን ከዜግነት ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሄድኩባቸው ተቋማት ነበሩ፡፡ ክፍያ የሚከፈልባቸው ቦታዎች ላይ ዘመኑ ያመጣቸው የቴክኖሎጂ አማራጮች አሉ፡፡ ከእነዚህ አንዱ ቴሌ ብር ነው፡፡ በቴሌ ብር ክፍያዬን ከፍየ ለፈጣን አገልግሎታቸው አመስግኜ ወጣሁ፡፡ እዚህ ቦታ ላይ በቴሌ ብር የሚከፈለው በፍላጎት ነው፤ በጥሬ ገንዘብ የመክፈል አማራጩም አለ ማለቴ ነው፡፡

ለሌላ ጉዳይ ሌላ ቦታ ስሄድ ደግሞ ክፍያው በሞባይል ባንኪንግ ወይም በቴሌ ብር መሆኑ አስገዳጅ ነው። ከወራት በፊትም እንዲህ አይነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም አጋጥሞኛል፤ ተቋሙ በብዙ ሺህ (በሚሊዮንም ሊሆን ይችላል) ሰዎች ስለሚያስተናግድ ለጥሬ ብር አከፋፈል አይመችም፡፡

በእነዚህ አሠራርን በሚያቀላጥፉ የቴክኖሎጂ አማራጮች እያመሰገንኩ ሳለሁ፤ እዚያው ቦታ ላይ ግን የሚያማርሩ ሰዎችን አየሁ፡፡ ለምን በጥሬ ብር አልሆነም ነው ወቀሳቸው፡፡ የሚገርመው የሚያማርሩትና የሚገላምጡት በብዛት የተማሩ ናቸው፤ የያዙት ስልክ የመስኮት በር የሚያክል ነው፡፡ በተደጋጋሚ የሚያነሱት ወቀሳ ግን ለምን በሞባይል ባንኪንግ ወይም በቴሌ ብር ሆነ የሚል ነው፡፡ በፈለጉት መንገድ መክፈል መብት መሆኑን ነው። በቴክኖሎጂ አማራጮች መደረጉ ጭቆና እንደሆነ አድርገው ነው፡፡

እነዚህ የቴክኖሎጂ አማራጮች ለጊዜው ሁሉም ሰው ሊጠቀማቸው አይችልም፤ መጠቀም የማይችሉ ሰዎች እንደሚኖሩም ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ አስገዳጅ መሆናቸው ለጊዜው ልክ ነው ልክ አይደለም የሚለው ማከራከሩ አይቀርምና ልክ ነው ልክ አይደለም የሚለውን እንለፈው። በዚህ አጋጣሚ ግን ሰብዓዊ መብት ከሥልጣኔ ጋር የሚሄድ መሆኑን ልብ እንበል፡፡

‹‹መብቴ ነው›› የሚባሉ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ መብት ግን ተግባራዊ የሚሆነው ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ አንድ ሰው ከሺህ እና ከመቶ ዓመታት በፊት የነበሩ ነገሮችን ዛሬ ላይ መጠቀም መብቴ ነው ቢል ነባራዊ ሁኔታው አይፈቅድለትም፡፡ ለምሳሌ፤ ማመልከቻ የማስገባው በብራና ነው ብሎ ድርቅ ቢል አይሆንም፤ ምክንያቱም በዚህ ዘመን በብራና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም የለም፡፡ አንድ ተቋም ማመልከቻ የምቀበለው በኢሜል ወይም በቴሌግራም ነው ብሎ ቢያሳውቅ፤ ‹‹አይ! እኔ በወረቀት ብቻ ነው ማስገባት የምፈልገው›› የሚል ሰው ቢኖር መብቱ አይሆንም ማለት ነው፡፡ መብቱ የሚሆነው በተፈቀዱ ነገሮች ላይ ነው፤ መብቱ የሚሆነው የዘመኑ እና የአካባቢው (የተቋሙ) ነባራዊ ሁኔታዎች በሚፈቅዱት ነው፡፡

ነገሩን ሰፋ አድርገን ካየነው ሰብዓዊ መብት የሚባለው ራሱ ከሥልጣኔ ጋር የሚሄድ ነው፡፡ ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት የነበረው የሰው ልጅ ሁኔታ እና ዛሬ ላይ ያለው የሰው ልጅ ሁኔታ ልዩነቱ ሰፊ ነው፤ ሌላ ፍጥረት እና ሌላ ፍጥረት እንደማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ በዋሻ ውስጥ ይኖር የነበረበት ዘመን እና ዛሬ ጨረቃ ላይ የሚኖርበት ዘመን ልዩነቱ የሌላ ፍጥረት እና የሌላ ፍጥረት ያህል ነው፡፡ ስለዚህ ሰብዓዊ መብት ከዘመን ዘመን እየሰፋ እና እየተለወጠ ነው የሚሄደው። ከዘመን ዘመን ብቻ ሳይሆን ከሀገር ሀገር ይለያያል፤ የሠለጠነ ሀገር ሰብዓዊ መብት እና ያልሠለጠነ ሀገር ሰብዓዊ መብት በእጅጉ ይለያያል፡፡

ለምሳሌ፤ በሠለጠነው ዓለም በባዶ እግር መሄድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው፡፡ የቆሸሸ ልብስ መልበስ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው፡፡ ጥራቱን ያልጠበቀ ምግብ መመገብ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው፡፡ በድሃ እና በኋላቀር ሀገራት ግን የወዳደቀ ምግብ ማግኘት ራሱ ቅንጦት ሊሆን ይችላል፡፡ የቆሸሸ ልብስ ማግኘት በራሱ ምናልባትም እንደ ዕድለኛነት ሊታይ ይችላል። በሠለጠነው ዓለም የጉልበት ብዝበዛ የሚባለው ነገር በድሃ እና ኋላቀር በሆኑ ሀገራት ደግሞ ‹‹ምነው ሰውነቴ እስከሚቆስል በሠራሁና በበላሁ›› የሚባልበት ሊሆን ይችላል፡፡

ለዚህም ነው በአውሮፓ ሀገራት እና በአፍሪካ ሀገራት መካከል ያለው የሰብዓዊ መብት አያያዝ እጅግ የተለያየ የሆነው፡፡ ዓለም አቀፍ ተቋማት በየጊዜው በአፍሪካ ሀገራት መንግሥታት ላይ የሚያወጧቸው ሪፖርቶች በአፍሪካ የሰብዓዊ መብት እንደማይከበር የሚገልጽ ነው፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ ተቋማት የመለኪያ መስፈርቶቻቸው የሠለጠኑት ሀገራት ናቸው። የአንዲት ልጃገረድ ኩበት መልቀም ለእነርሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው፤ በድሃ አገር ውስጥ ግን የዕለት እንጀራዋ ነው፡፡ ያንን ሥራ ለመተው የሚያስችላት ምቹ ሁኔታ የለም፡፡

ድሃ እና ኋላቀር መሆን በራሱ የዘመኑን ሰብዓዊ መብት የጣሰ ነው፡፡ መንግሥት ወይም ሌላ አካል ባያፍን እንኳን ሁኔታው በራሱ ሰብዓዊ መብትን የጣሰ ነው፡፡ እንደ ሰው መኖር ያለበትን ነገር መኖር አይችልም፣ እንደ ሰው ማግኘት ያለበትን ነገር አያገኝም፡፡ ሌላው ይቅርና በጤና የመኖር መብታችንን እንነፍጋለን፡፡ ያለመረበሽ መብታችንን እንነፍጋለን። በመጥፎ ሽታ ለመታመም ሁኔታዎች አስገዳጅ ናቸው፣ በኃይለኛ ጩኸትና ጫጫታ ለመረበሽ የነገሮች አለመሠልጠን ያስገድዳል፡፡

በእነዚህ ሁኔታዎች ሰብዓዊ መብት የሚባለው የዚያ ዘመን ሰው የሚኖርበት መብት ማለት ነው፡፡ የዚያ ሀገር ሰው የሚኖርበት ሁኔታ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አንድን ነገር በግድ መጫንም ሰብዓዊ መብት ጥሰት ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንዲት ከገጠር አካባቢ የመጡና ስለቴክኖሎጂ ምንም የማያውቁ እናት በቴሌ ብር ካልሆነ የፈለጉትን አገልግሎት ማግኘት አይችሉም ብሎ መከልከል የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ የማያገናዝብ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም በሀገሪቱ ውስጥ ብዙ መጻፍና ማንበብ የማይችል ማኅበረሰብ አለ፡፡ ስለዚህ ሰዋዊ መብት ሲባል የዚያች ሀገር ሰዎች መብት ማለት ነው፤ የግድ ከአውሮፓ ሀገራት ሰዎች ጋር ሊመዘኑ አይገባም፡፡

ሰብዓዊ መብቶቻችን ይከበሩልን ዘንድ ሥልጣኔን እንለማመድ፡፡ ሥልጣኔ ማለት የ100 ሺህ ብር ስልክ መያዝ አይደለም፡፡ ሥልጣኔ ማለት የዘመኑ ሰዎች የደረሱበት የአስተሳሰብና የዕውቀት ደረጃ ላይ መድረስ ነው፡፡ ይህ እንደ መንግሥትም እንደ ግለሰብም ልናደርገው የሚገባ ነው፡፡ መንግሥት አስገዳጅ ደንቦች ማውጣት ብቻ ሳይሆን ‹‹ምን አይነት ዜጋ ነው ያለኝ? የት ድረስ አስተምሬያለሁ? ምን ያህል ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሬያለሁ?›› ብሎ ማሰብ አለበት፡፡

እንደ ግለሰብ ደግሞ ዘመኑ የሚጠይቃቸውን ነገሮች መላመድ አለብን፡፡ ከዘመኑ ጋር ካልሄድን አሠራሮችና ሕጎች ዘመንን ተከትለው ይቀየራሉ፡፡ ለምሳሌ፤ ከዓመታት በፊት አድራሻ የሚነገረው ‹‹ይህን ያህል ሜትር ገባ ብሎ፣ ከምንድንትስ ፊት ለፊት...›› እየተባለ ነበር፡፡ አሁን ግን ድረ ገጽ ብቻ ሊነገር ይችላል። ብዙ ተቋማት የምዝገባ ማስታወቂያ ሲያወጡ በድረ ገጽ ብቻ መሆኑን ያሳውቃሉ፡፡ ስለዚህ አሠራሮች ተቀየሩ ማለት ነው፡፡ አንድ ኢንተርኔት መጠቀም የማይችል (የማይወድ) ሰው ቢኖር አገልግሎቱን ማግኘት አልቻለም ማለት ነው፡፡ ለእሱ ተብሎ የተለየ የአሠራር ሕግ አይወጣም፡፡ የማይሆንን ነገር መብቴ ነው ማለት አያስኬድም፤ መብት በአስገዳጅ ሁኔታዎች ይገደባል፤ የአንድ ሰው መብት በሌላ ሰው መብት ይገደባል፡፡

በአጠቃላይ፤ ዘመናዊውን ሰዋዊ መብት ለመጠቀም ዘመናዊ እንሁን፤ መንግሥትና ተቋማትም የምትመሩትን ሀገርና ሕዝብ ነባራዊ ሁኔታ አገናዝቡ!

# ዓለም አቀፍ

## ተፈጥሮን መጠበቅ ዓለምን ከ2 ነጥብ 7 ትሪሊየን ዶላር ኪሳራ ይታደጋል- ዓለም ባንክ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ተፈጥሮን ከአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎች መጠበቅ ዓለምን በ2030 ከ2 ነጥብ 7 ትሪሊየን ዶላር ኪሳራ ያድናል ሲል ዓለም ባንክ ገለፀ።

በባንኩ የአየር ንብረትና የተፈጥሮ ሃብቶች ዳይሬክተር ቫለሪ ሂኪ ከኤምሬትስ የዜና ወኪል ዋም ጋር ባደረጉት ቆይታ፥ የአየር ንብረት ለውጥ በሀገራት ምጣኔ ሃብታዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እያደረሰ መሆኑን ተናግረዋል።

በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት ተጎጂ መሆናቸውን በመጥቀስ ሀገራቱ በ2030 ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርታቸው (ጂዲፒ) ውስጥ 10 በመቶውን በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እንደሚያጡ በጥናት መረጋገጡን አብራርተዋል።

ደኖች እና የውሃማ አካላትን ብዝሃ ሕይወት መጠበቅ ካልተቻለ የሀገራት ምጣኔ ሃብታዊ እድገት ክፉኛ እንደሚፈተንም ነው የጠቆሙት።

በተፈጥሮ ሃብቶች ላይ የሚደርሰው አደጋ በሰው ልጆች ጤና፣ ምግብ ዋስትና፣ የኃይል ፍላጎት እና ሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ተፅዕኖው እየበረታ ስለሚሄድ ሀገራት ተፈጥሮን ለመጠበቅ መትጋት እንዳለባቸውም ዳይሬክተሯ አሳስበዋል።

ዓለም ባንክም ተፈጥሮን መጠበቅ ለመሠረተ ልማት ማስፋፋትም ሆነ ዘላቂ



ዓለም ባንክ የአየር ንብረት ለውጥን ለሚቀንሱ ሥራዎች የሚያቀርበውን ብድር ወደ 9 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ለማድረግ ቃል ገብቷል

እድገት ለማስመዝገብ ወሳኝ መሆኑን በማመን የአየር ንብረት ለውጥን ለሚቀንሱ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ድጋፍ እያደረገ ነው ብለዋል።

በኮፕ28 ጉባኤ ዓለም ባንክም የአየር ንብረት ለውጥን ለሚቀንሱ ሥራዎች የሚያቀርበውን ብድር በ2024 እና 2025 ወደ 9 ቢሊየን ዶላር ከፍ ለማድረግ ቃል ገብቷል።

ሌሎች ዓለማቀፍ የፋይናንስ ተቋማትም የአየር ንብረት ለውጥን ለሚቀንሱ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ 22 ነጥብ 6 ቢሊየን ዶላር ለማቅረብ ከስምምነት መድረሳቸው የሚታወስ ነው።

## ተመድ 180 ሚሊዮን ገደማ ሕዝብ ለመርዳት የሚውል ፈንድ ለመሰብሰብ ማቀዱን ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ተመድ 180 ሚሊዮን ገደማ ሕዝብ ለመርዳት የሚውል ፈንድ ለመሰብሰብ ማቀዱን ገለጸ፡፡

ተመድ በ2024 በግጭት፣ በአየር ንብረት ለውጥ እና በኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የተጎዳ 180 ሚሊዮን ሕዝብ ለመርዳት የ46.4 ቢሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ አቅዷል።

ትኩረት የተደረገው በእስራኤል እና ሀማስ ጦርነት ላይ ቢሆንም፣ ተመድ ባወጣው መግለጫ ግን እንደ ሱዳን እና አፍጋኒስታን ያሉ ሀገራት ወሳኝ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ብሏል።

“የሰብዓዊ ሠራተኞች ሕይወት ያድናሉ፣ ረሃብን ይዋጋሉ፣ ሕጻናትን ይጠብቃሉ፣ ከወረርሽኝ ይከላከላሉ” ያሉት የተመድ የሰብዓዊ ጉዳዮች አስተባባሪ ማርቲን ግሪፊትስ ነገር ግን ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በቂ ድጋፍ እያቀረበ አለመሆኑን ተናግረዋል።

ዓለምቀፍ ተቋማት ለእርዳታ የሚውል በቂ ፈንድ አለማግኘት ከፍተኛ ቀውስ ያስከትላል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

ተመድ በ2023፣ 56.7 ቢሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ አቅዶ የነበረ ቢሆንም መሰብሰብ የተቻለው 35 በመቶውን ብቻ



ነው።

የተመድ ኤጀንሲዎች 128 ሚሊዮን ለሚሆን ሕዝብ ድጋፍ እና ጥበቃ ያደርጋል።

2023 ከ2010 ወዲህ ዓለምአቀፍ እርዳታ የቀነሰበት ዓመት መሆኑ ተገልጿል።

ተመድ ለ2024 ያቀረበውን የገንዘብ ጥያቄ ዝቅ በማድረግ አስቸኳይ ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው ላይ ትኩረት አድርጓል።

ተመድ ድጋፉን ከ72 ሀገራት ለመሰብሰብ አቅዷል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# 88 ዓመታት ኢትዮጵያን በመታደግ

ክብረዓብ በላቸው



ኢትዮጵያ የኩሩ ሕዝብና የጀግኖች ሀገር ነች ሲባል በግምት አይደለም። ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የኖረው የአርነትና ተጋድሎ ታሪካችን ምንጊዜም ስለሚዘከር ነው። ኢትዮጵያ ዘመናዊ የጦር ኃይል መገንባት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በዋንኛነት ከሚጠቀሱት የጦሩ ክፍሎች አንዱ የኢፌዴሪ አየር ኃይል ነው። አየር ኃይሉ ከተመሠረተበት ከኅዳር 20 ቀን 1928 ዓ.ም. ጀምሮ የሀገርን የአየር ድንበር ከመጠበቅ አንስቶ በተለያዩ የውጊያ ዓውዶች ከፍተኛ ጀብዱዎችን በመፈጸም ለሀገርና ለሕዝብ የኩራት ምንጭ የሆነ ተቋም ነው።

ከምሥረታው እስከ 1942 ዓ.ም በንጉሡ ቀጥታ አመራር በሲዊዲናዊዎቹ ጄኔራል ሐርድና ካውንት ቮን ሮዛን (ኮሎኔል) አማካሪነት ሥራውን የጀመረው አየር ኃይሉ፤ ከምሥረታው ማግስት ጀምሮ በሙያው አንቱታ ባተረፉ እንደ ሜ/ጄ አሰፋ አያና፣ ሜ/ጄ አበራ ወ/ማርያም፣ ሜ/ጄ ፋንታ በላይ እና ሜ/ጄ አምሐ ደስታ የተመራ ባለብዙ ገድል ተቋም ነው።

እንደ እ.ኤ.አ. በ1935 በጣሊያን ወረራ ወቅት የኢትዮጵያ አየር ኃይል የነበሩት አራት አብራሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሥራ ሦስት አውሮፕላኖችና ጥቂት የማጓጓዣ አውሮፕላኖችም ነበሩት። ከእ.ኤ.አ ከ1934 እስከ 35 አውሮፕላኖቹ ለአምቡላንስ ሥራ ጭምር ያገለግላሉ ነበር። አየር ኃይሉ እስከ 1935 በኮሎን ጆን ሮቢንሰን (አፍሪካዊ አሜሪካዊ) ነበር ይታዘዝ የነበረው።

ፋሺስት ኢጣሊያ በዳግም ወረራው ወቅት አየር ኃይሉን በኢትዮጵያውያን አርበኞች ላይ በዓለም አቀፍ ሕግ የተከለከለን የጦር መሣሪያ ሳይቀር ተጠቅሞ በሀገሪቱ ላይ አደገኛ ተፅዕኖ ያለው የሰው እና የእንስሳት ሕይወት የቀጠፈ ጉዳት አስከትሏል። ንጉሥ ኃይለስላሴ ከስደት ከተመለሱ በኋላ ከጣሊያን ትምህርት በመውሰድ የአየር ኃይል በጦርነት ውስጥ ያለውን ጨዋታ ቀያሪ ሚና በመገንዘብ አየር ኃይሉን ደግም ለማደራጀት ጥረት አድርገዋል።

በወቅቱ ንጉሡ እኤአ በ1946 ከአሜሪካና ከታላቋ ብሪታንያ ባገኙት ወታደራዊ እርዳታ ጥቂት አውሮፕላኖችና የበረራ ትምህርት ቤት መቋቋም ችለው ነበር፡፡ በኋላ ግን አሜሪካም ሆነች ታላቋ ብሪታንያ የኢትዮጵያን አየር ኃይል ለመደገፍ ባለመፈለጋቸው ንጉሡ ፊታቸውን ወደ ስዊድን በማዞር ዘመናዊ አየር ኃይል ለመገንባት ጥረት ማድረግ ችለዋል።

የአየር ኃይሉ ከሀገር ውስጥ ግዳጅ ባለፈ በዓለም አቀፍ የሠላም ማስከበር ሥራዎች ላይ በመሳተፍ አንቱታን ያተረፈ ነው ። ለዚህም በ1960 ዓ.ም በአራት ኤፍ 86 አውሮፕላኖች በፍላይት ደረጃ ኮንጎ ዛየር በተደረገው የሠላም ማስከበር ሥራ ላይ በቀዳሚነት ተሳትፏል። 2000 ዓ.ም ዳርፉር ሱዳን (UNAMID) በኦቭዬሽን የሰላም ማስከበር ዩኒት በአምስት ሚ- 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተሮች ከተሟላ የጥገና አቅምና የድጋፍ መሣሪያዎች ጋር ተሰማርቷል። በአብየና ሩዋንዳ የሎጅስቲክና ጦር ማዘዋወር ግዳጆችን በብቃት መወጣቱን መጥቀስ ይቻላል።

የቀድሞው የሶማሊያ አምባገነናዊ መሪ ዚያድ ባሬ በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል የከፈተውን የመስፋፋት ጦርነት በብቃት እና በታላቅ ተጋድሎ ለመከላከል በተደረገው ጦርነት አየር ኃይሉ ከፍ ባለ ብቃት የፈጸማቸው ጀብዱዎች የሀገሪቱን ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ሂደት የጎላ ስፍራ ከመያዝ ባለፈ፣ ተቋሙና ባለሙያዎቹ የብዙ ጀብዱ ትርክቶች ባለቤት እንዲሆኑ አድርጎታል።

ሶማሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ጊዜውና አጋጣሚውን መርጣና ተደራጅታ ነበር፡፡ ጃንሆይ ከሥልጣን እንደወረዱ ደርግም ገና ምኑን ልያዘው፤ ምኑን ልጨብጠው በሚልበት ጊዜ በአጠቃላይ በዚያን ወቅት ኢትዮጵያ የነበራት አራት ክፍለ ጦር ብቻ ነበር።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል በዚያን ዘመን ለማጓጓዥ ዳኮታና ሲ-42 የተባሉ የአሜሪካን አውሮፕላኖች እንዲሁም ኤፍ-5 የተባለ ተዋጊ ጄት የታጠቀ ነበር። ከንጉሡ ከሥልጣን መውረድ በኋላ ኢትዮጵያ በዚህ ሁኔታ ባለችበት ወቅት ነው የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ዚያድ ባሬ ከሶቪየት ኅብረት እጅግ ዘመናዊ የተባሉትን ሚግ 21፣ ሚግ 23 የጦር ጄቶችን እና ሚ-17 የመሳሰሉትን ተዋጊ ሄሊኮፕተሮች ፤ ቲ-55-57 ታንኮችን፤ 120 ሚሜ መድፎችን ቢ ኤሞችን ብረት ለበሶችን ጊዜ ወስዶ፣ ታጥቆና ተደራጅቶ በሚገባም አሠልጥኖ፤ ነበር ወረራ የፈፀመው፡፡ በዚህ ጦርነት ታዲያ አየር ኃይሉ የፈፀመው ጀብዱ ታላቅ ነበር።

የኢፌዴሪ አየር ኃይል በንጉሡ ዘመን ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገትና መሻሻል እያሳዬ ነበር። ለእዚህ ማሳያው የውጊያ ችሎታና የበረራ ትርዒት ላይ አስገራሚ ብቃት ያላቸው አብራሪዎች መታየታቸው ነበር። በ1960ዎቹ መጀመሪያ የነበሩ የንጉሠ ነገሥቱ አየር ኃይል አብራሪዎች ብዛት ባላቸው አውፕላኖች የአየር ትርዒት ማሳየት የተለመደ ነው። በአንድ ወቅት ንጉሡ በክብር እንግድነት ሲገኙ አብረዋቸው የነበሩት የኬንያው ፕሬዚዳንት ጆሞ ኬንያታ «የኢትዮጵያን ነፃነት በሚገባ የሚጠብቅና በቂ ዋስትና ያላችሁ ለመሆኑ ይህ ዓይነተኛ ምስክር ነው። ስለዚህም ዓይነ ሥውር ካልሆነ በቀር የኢትዮጵያን ነፃነት ለመድፈር የሚመጣ ይኖራል ብዬ አላምንም» ማለታቸውን ከአየር ኃይል የተገኙ ሰነዶች ያስረዳሉ።

የአየር ኃይል የኦቭዬሽን ጥገና አቅሙ መጐልበትም በጥንካሬ የሚነሳ አቅም ነው። ምንም እንኳን የጥገና ተቋሙ ከ1921 ጀምሮ በውጭ ሀገር ዜጐች ጭምር አገልግሎት ሲሰጥ ቢቆይም 1970ዎቹ ገደማ መዳከም አሳይቷል። በተለይ «የሶቭዬት ኅብረት ትጥቆች ወደ ሀገራችን መግባታቸውን ተከትሎ አውሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች ብልሽት ሳያጋጥማቸው ውጭ ሀገር ልኮ ማሠራት የተለመደ ነበር።» ይላሉ ለረጅም ዓመታት በኢትዮጵያ አየር ኃይል የሠሩ ኃላፊዎች።

ጦርነት ሲቀሰቀስ አንድ በሰላሙ ጊዜ በሚገባ የተማረ የሠለጠነ የተደራጀ አሰላለፉን ጠንቅቆ የሚያውቅ ኃይል ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ዓይነት አይሆንበትም፡፡ ሌላው የመጎልበት መለኪያ የመከላከያ ኃይሉ በእጁ የያዛቸው የታጠቃቸው ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ናቸው

ከአየር ኃይል የወጣ የጽሑፍ መረጃ እንደሚያስረዳውም በ1982 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ የውስጥ ጥገና አቅም በመዳከሙ የማይሠሩ አውሮፕላኖች በዝተው ነበር። ለምሳሌ ከነበሩት 48 ሚግ 21 አውሮፕላኖች መካከል ለውጊያ ዝግጁ የነበሩት 6 ብቻ ነበሩ።

ከደርግ መንግሥት ውድቀት በኋላ ሥልጣን የያዘው በሕወሓት የሚመራው የኢሕአዴግ መንግሥት አየር ኃይሉን እንደገና ለማደራጀት በሚል አፍርሶ ብዙ አንጋፋ አብራሪዎች አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ምክንያት ሆኗል። በ2010 ወደ ሥልጣን የመጣውና በጠቅላይ ሚኒስትር ዓቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሚመራው መንግሥት ለተቋሙ በሰጠው ልዩ ትኩረት አየር ኃይል እንደገና ተደራጅቶ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በአየር ለመጠበቅ ዝግጁ መሆን ችሏል።

በሂደት ሲዳከም ቆይቶ አየር ኃይል ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ትንሳኤውን አግኝቷል፡፡ ከአየር ኃይል የጥገና ማዕከል ባሻገር ዛሬ በደጀን አቭዬሽን የሚሠሩ (የሚጠገኑ) አውሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች ከሀገር አልፈው እንደ ሱዳን አንጎላና ደቡብ ሱዳንን ጭምር እያገለገሉ ነው። በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የአውሮፕላንና ሄሊኮፕተር ሞተሮችና ክንፎችን እንዲሁም የውስጥ ክፍሎች በጥራት ይጠገናሉ። «የኦቨር ሆል» ጊዜ ገደብ የማራዘም ሥራ የሞዲፊኬሽንና የፈጠራ ሥራዎች ይከናወናሉ።

የኢፌዴሪ አየር ኃይል ሲቋቋም የነበሩት የአየር ምድቦች የማዕከሉን ደብረ ዘይት ምድብ ጨምሮ በአሥመራ በድሬዳዋና በሐረር ነበር። ከደርግ ውድቀት በኋላ መቀሌና ባሕርዳር ተጨምሮ አሁን በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫ የአየር ምድቦች ተቋቁመዋል። በእዚህም ሀገሪቱን ከማንኛውም የአየር ጥቃት የሚጠብቅ የ24 ሰዓት ተጠንቀቅ ያለው አቅም ስለመገንባቱ ከአየር ኃይል የሚወጡ መረጃዎች ያስረዳሉ።

የአየር ኃይል የማዕከል ምድቡ ግቢ (ቢሾፍቱ) ሞቃታማ ቢሆንም አረንጓዴ የሞላበትና ፅዳት የማይለየው ነው። ይህንን አንጋፋ የሀገር ባለውለታ ተቋም የተለያዩ የሀገር መሪዎች ጎብኝተውታል፡፡ ከእንግሊዛዊቷ ንግሥት ኤልሳቤጥ ጀምሮ የቤልጅየሙ መሪ፤ የኩባው መሪ ፊደል ካስትሮ፣ የጋናው መሪ ጀሪ ሮሊንግ የኮንጐው ሞቡቱ ሴ ሴ ሴኮን ጨምሮ ሌሎችም በተለያየ ጊዜ የነበሩ የተለያዩ የሀገር መሪዎች ጎብኝተውታል። አድናቆታቸውንም ቸረውታል፡፡

በአንድ ወቅት ስመገናና የነበረው የኢትዮጵያ አየር ኃይል በመሐል መዳከም ቢታይበትም ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ድንቅ ግስጋሴ እያስመዘገበ ይገኛል። የበረራ አቅሙን ወቅቱ እስከደረሰበት ቴክኖሎጂ በማሳደግ ያለውን ነባር አቅም (ሀብት) በመጠንና በጥራት በማሻሻል የሰው ኃይሉን በስፋት በማልማት ላይ ይገኛል። ከእነዚህ ሀገራዊና ሕገመንግሥታዊ ኃላፊነቶቹ ባሻገር በማኅበራዊ ዘርፍም ሰፊ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል።

በስፖርቱ ዘርፍ አየር ኃይል አንጋፋው ሻምበል ምሩፅ ይፍጠርን ጨምሮ በርካታ አትሌቶችን አፍርቷል። በእግር ኳስ ስፖርትም አየር ኃይል ስም ያለው ክለብ የነበረውና(ንብ)የሚል ቅፅል ስያሜ የተሰጠው የእግርኳስ ቡድን እስከ አሁንም የቀጠለ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ሊግ ጥሩ ተፎካካሪ ሆኖ ይገኛል። ሌላው በአካባቢ ጥበቃና የልማት ሥራዎች ረገድ በተለይ የአየር ምድቦች በሚገኙበት አካባቢ ካለው ማኅበረሰብ ጋር ተቀናጅቶ እየሠራ ያለ ተቋም እንደሆነ ይነገራል።

በደብረዘይት (ቢሾፍቱ) አየር ኃይል አካባቢ የሚኖሩ የከተማዋ ነዋሪዎችም ለተቋሙ ያላቸው ፍቅር በተለያየ ጊዜ ይገልፃሉ «አየር ኃይልና ደብረዘይት ተነጣጥለው አይታዩም። እንዲሁ ደግሞ በአካባቢ ልማትም ሆነ በአደጋ የተጎዱ ወገኖችን ለመርዳት አየር ኃይል የተለያየ ተሳትፎ ያደርጋል።

ቀደም ሲል የአየር ምድቡ ከከተማ ዳርቻ የተሠራ ቢሆንም አሁን በከተማዋ መስፋፋት አንዳንድ መኖሪያ ቤቶች ተጠግተውታል። አንዳንዶች የአውሮፕላንና ሄሊኮፕተር ድምፆች ዘወትር ቢጮኹም ስለለመዱት የሚሰለቻቸው አይደለም። ከተቋሙ መስፋፋትና መጠናከር ጋር ተያይዞ በሚፈጠረው የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚጠቀሙ፣ በሚፈጠረው የሥራ ዕድል ሕይወታቸውን መምራት የጀመሩ የአካባቢው ነዋሪዎችም አየር ኃይልን ይበልጥ የኩራታቸው ምንጭ ማድረግ ችለዋል። በአጠቃላይ አንጋፋው የኢፌዴሪ አየር ኃይል ከትናንት እስከ ዛሬ ብዙ ውጣውረዶችን አልፎ እነሆ እዚህ ደርሷል።

የአንድ መከላከያ ኃይል እምቅ አቅምና ጥንካሬ፤ የመለኪያ መስፈርቶቹ፤ የሠራዊቱ ብቃትና የውጊያ ዝግጁነት የታጠቀው ዘመናዊ የጦር መሣሪያና በታጠቀውም መሣሪያ በየትኛውም የመሬት ገጽ ላይ ለመጠቀም ያለው ችሎታና ብቃት ሀገርን ለመከላከል በውስጥ በተለያዩ ዓውደ ውጊያዎች ተሰልፎ ያስመዘገበው ድልና ስኬት ከዚህም አልፎ ድንበር ዘለል ተልዕኮን በመወጣት ረገድ (ዓለም አቀፍ) ያሳየው ወይንም የሚያሳየው ብቃት የአቅሙን ልኬት ሊያሳዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

አንድ የመከላከያ ኃይል ያለው የውጊያ ብቃትና ችሎታ የሚገነባው በሰላሙ ጊዜ በሚሰጠው ተደጋጋሚና የማያቋርጥ በተለያዩ ከግዳጅ አፈጻጸሙ ጋር ሊያጋጥሙት በሚችሉት ተመሳሳይ የመሬት ገጽታ ዓይነቶች ላይ በሚያደርገው ሥልጠና ከዚህም ባሻገር የተናጠል ሳይሆን የጣምራና የተቀናጀ የጦር ልምምዶችን በየሙያ መስኩ ያደርጋል፡፡

ጦርነት ሲቀሰቀስ አንድ በሰላሙ ጊዜ በሚገባ የተማረ የሠለጠነ የተደራጀ አሰላለፉን ጠንቅቆ የሚያውቅ ኃይል ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ዓይነት አይሆንበትም። ሌላው የመጎልበት መለኪያ የመከላከያ ኃይሉ በእጁ የያዛቸው የታጠቃቸው ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ናቸው።

ኢትዮጵያ በተፈተነችበት ጊዜ ሁሉ ሉዓላዊነቷን ለማስከበር በጀግንነት ከተፋለሙ የሀገር መከላከያ ክፍሎች አየር ኃይል ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል ብንል ማጋነን አይሆንም። ይህ አንጋፋና የአፍሪካ ተምሳሌት የሆነው አየር ኃይል ከኅዳር 20 2016ዓ.ም ጀምሮ 88ኛ የምሥረታ በዓሉን እያከበረ ይገኛል። የምሥረታ በዓሉን በመጪው ታኅሣሥ 6 ቀን 2016 ዓ.ም በተለያዩ ዝግጅቶች በማጠቃለያ መርሐግብር እንደሚያከብር አስታውቋል።

የአየር ኃይል ምሥረታ በዓል ታሪካዊ አመጣጡን በጠበቀ መልኩ ይከበራል ያሉት የወቅቱ የአየር ኃይል አዛዥ ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ፤ ይህ ዝግጅት ለመጀመሪያ ጊዜ ለግዳጅ ብቁ አብራሪዎችን ማስመረቅን ጨምሮ በፓናል ውይይት፣ ለሕዝብ ክፍት በሚሆኑ ጉብኝቶችና ሌሎች ዝግጅቶች እንደሚከበር ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አብራርተዋል።

የአዲስ ዘመን የዝግጅት ክፍልም መላው ኢትዮጵያውያንን ለዚህ የሀገር ባለውለታና መኩሪያ ለሆነ አንጋፋ ተቋም የ88ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል እንኳን አደረሳችሁ አደረሰን ይላል።

# ስፖርት





## ከሰባት ዓመት በኋላ የተገኘ ሰባተኛው ታላቅ ድል

**ቦጋለ አበበ**

የዓለም አትሌቲክስ በየዓመቱ ድንቅ አቋም ያሳዩ አትሌቶችን አወዳድሮ በደማቅ ሥነሥርዓት ይሸልማል። ይህን ታላቅ ሽልማት ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ እኤአ በ1999፤ ቀነኒሳ በቀለ በ2004 እና በ2005፣ መሠረት ደፋር በ2007፣ ገንዘቤ ዲባባ በ2015 እንዲሁም አልማዝ አያና በ2016 ያሸነፉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው። ከአልማዝ አያና በኋላ ግን ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ባለፉት ሰባት ዓመታት ሽልማቱን ማሸነፍ አልቻሉም። በነዚህ ዓመታት ለሽልማቱ የታጩ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም እጅግ ጥቂት ናቸው፡፡


በውድድር ዓመቱ በአንድ የማራቶን ውድድር ብቻ ለማመን የሚከብድ ድንቅ ብቃት በማሳየት ክስተት የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትዕግስት አሰፋ ትልቁን የዓለም አትሌቲክስ ሽልማት ከሰባት ዓመት በኋላ በማሸነፍ ሰባተኛዋ ኢትዮጵያዊ አትሌት መሆን ችላለች። ትዕግስት በ2023 የውድድር ዘመን በማራቶን ያስመዘገበችው የላቀ ውጤት ለሽልማቱ አብቅቷታል። ባለፈው መስከረም የበርሊንን ማራቶን ያሸነፈችበት 2:11:53 አዲስ የዓለም ማራቶን ክብረወሰን ሲሆን፣ ቀድሞ ከነበረው ክብረወሰን በ2 ደቂቃዎች ከ14 ሰከንዶች የተሻለና ሰፊ ልዩነት ያለው ነው። የሴቶችን ማራቶን የዓለም ክብረወሰን ያሻሻለች የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት የሆነችው ትዕግስት ሽልማቱን ለማሸነፍ በአንድ ውድድር ብቻ ያሳየችው ለማመን የሚከብድ ብቃት በቂ ሆኗል፡፡

በተመሳሳይ ባለፈው ቅዳሜ የ10ሺ ሜትር የዓለም ሻምፒዮና የብር ሜዳሊያ አሸናፊዋ አትሌት ለተሰንበት ግደይ የዓመቱ የስፖርታዊ ጨዋነት ሽልማት አሸናፊ መሆኗ ይታወሳል። የዓለም አትሌቲክስ በየዓመቱ በሚያካሂደው ሽልማት አንዱ ዘርፍ የስፖርታዊ ጨዋነት ሲሆን ኢትዮጵያዊቷ ኮከብ ለተሰንበት በቡዳፔስት በተካሄደው የዓለም ሻምፒዮና በሴቶች 10ሺ ሜትር ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከአንድ እስከ ሦስት ሲያጠናቅቁ የብር ሜዳሊያ ማጥለቋ ይታወቃል፡፡

በዚያ ውድድር ወቅት በፉክክሩ መጨረሻ የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ጠንካራ ተፎካካሪ የነበረችው ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ የኔዘርላንድስ አትሌት ሲፈን ሃሰን ሜዳሊያ ለማጥለቅ ጥቂት ሲቀራት መውደቋ አይዘነጋም። በወቅቱ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀችው ለተሰንበት ባገኘችው ውጤት ደስታዋን ከመግለፅ ይልቅ ወደ ወደቀችው ሲፈን በመሄድ እጇ ላይ የደረሰውን ጉዳት እየተመለከተች ስታፅናናትና ማዘኗን ስትገልፅላት ታይታለች። ይህም ድርጊቷ የዓመቱን የስፖርታዊ ጨዋነት ሽልማት እንድታሸንፍ አድርጓታል።

የዓለም አትሌቲክስ ከትናንት በስቲያ ምሽት በፈረንሳይ ሞናኮ ባካሄደው የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ሽልማት ሥነሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ የሽልማት ዘርፎቹን ዘርዘር አድርጎ ሸልሟል። የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ሽልማት የዓለም አትሌቲክስ ከዚህ ቀደም ከተለመደው የወንድ እና ሴት አትሌቶች ጥቅል አሸናፊነት የሽልማት አሰጣጥ ዘርፍ በብዙ መንገድ ባሻሻለው መሠረት የዘንድሮ አሸናፊዎች በመም፣ በሜዳ ተግባራት እና ከስታዲየም ውጭ ውድድሮች በሚሉ ዘርፎች ምርጥ አትሌቶችን ሸልሟል።

በዚህም መሰረት በመም ውድድሮች የዓለም




ሻምዮኖቹ ኬንያዊቷ ፌይዝ ኪፕየጎን እና አሜሪካዊው ኖሃ ሊልስ የዓመቱ ምርጥ ሲባሉ፣ ስዊድናዊው ሞንዶ ዱፕላንቲስ እና ቬንዙዌላዊቷ ዩሊማር ሮሃስ ደግሞ የዓመቱ ምርጥ የሜዳ ተግባራት ውድድሮች አሸናፊዎች ሆነዋል።

ልክ እንደ ትዕግስት አሰፋ ሁሉ የዓለም የማራቶን ክብረወሰንን ቺካጎ ላይ 02:00:35 በሆነ ሰዓት ያሻሻለው ኬንያዊው ኬልቪን ኪፕቱም በበኩሉ የዓመቱ ከስታዲየም ውጭ ውድድሮች ምርጡ ወንድ አትሌት ሽልማትን አሸንፏል።

ኢትዮጵያዊቷ መዲና ኢሳ የመጨረሻ እጩ ተወዳዳሪ በነበረችበት የዓመቱ ተስፋ የሚጣልባት ታዳጊ አትሌት የሽልማት ዘርፍ ኬንያዊቷ ፌይዝ ቼሮቲች ስታሸንፍ በወንዶች ዘርፍም የሀገሯ ልጅ የሆነው የ800 ሜትር ተወዳዳሪው ኢማኑኤል ዋኒዮኒ አሸናፊ ሆኗል።

ትዕግስትና ኬንያዊቷ የ1500 ሜትር የዓለምና የኦሊምፒክ ቻምፒዮን አትሌት ፌይዝ ኪፕየጎን ይህን ሽልማት ሲያሸንፉ ከሰባት ዓመት በኋላ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን ሴት አትሌቶች ናቸው። ከፕዬጎን ይህን ሽልማት ስታሸንፍ የመጀመሪያዋ ኬንያዊት ሴት አትሌትም ነች።

በዚህ ሽልማት ላይ በውድድር ዓመቱ የዓለም ክብረወሰን በተለያዩ ርቀቶች ያሻሻሉ አትሌቶች በጃፓኑ ኤሌክትሮኒክስ አምራች ኩባንያ ‹‹TDK›› አማካኝነት እያንዳንዳቸው የመቶ ሺ ዶላር ተሸላሚ ይሆናሉ። የዓመቱ ምርጥ አትሌት በመባላቸውም ተጨማሪ ሰባ ሺ ዶላር ተሸላሚ ይሆናሉ።

## ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ ዕቃዎች እና ማሽነሪዎች ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 001/2016

የኢትዮጵያ ሴቶችና ህፃናት ልማት ድርጅት ያገለገለ ተሽከርካሪ ፣ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎችና ማሽነሪዎችን በጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል ፡፡

1. በጨረታው ለመወዳደር የሚፈልግ ማንነቱን የሚያረጋግጥ መታወቂያ በመያዝ እና የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን 22 አካባቢ ከሚገኘው የድርጅቱ ቢሮ መውሰድ ይችላል፡፡
2. ንብረቶቹን ማየት የሚፈልግ ጨረታው ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከሰኞ እስከ አርብ በስራ ሰዓት ቢሮ በመምጣት ማየት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለተሽከርካሪ ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ ብር) ፣ለቢሮ መገልገያ ጠረጴዛና ወንበርና መደርደሪያ ብር 2,000.00( ሁለት ሺህ ብር) ፣ ለኮምፒውተር ፕሪንተርና ተዛማጅ ዕቃዎች ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) እንዲሁም ለሚዲያ ዕቃዎች ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) በኢትዮጵያ ሴቶችና ህፃናት ልማት ድርጅት ስም( Organization for the Development of Women and Children) ስም በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ በተያያዘው የዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ ላይ የመወዳደሪያ ያቀረቡትን ዋጋ በአሀዝና በፊደል በመግለፅ እና በመፈረም በፖስታ በማሸግ እና በፖስታው ላይ ስማቸውንና የሚወዳደሩበትን ዕቃ በግልፅ በመፃፍ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ 10ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ድረስ የጨረታ ሰነዱን ማስገባት አለባቸው፡፡ ጨረታው በእለቱ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በ4፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ 10ኛው ቀን የእረፍት ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል፡፡
5. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዕቃዎች የአሸናፊነት ማሳወቂያ ደብዳቤ በደረሳቸው በ5 ቀናት ውስጥ ከፍለው ውል መዋዋል አለባቸው ፤ ይህ ሳይሆን ቢቀር ያስያዙት የጨረታ ዋስትና ገንዘብ ለድርጅቱ ገቢ ይሆናል፡፡
6. ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፡፡

ተጨማሪ መረጃዎችን በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የስልክ ቁጥር +251 11 18 50-12-37**
**22 አካባቢ ዮናስ ሆቴል ገባ ብሎ**
**የኢትዮጵያ ሴቶችና ህፃናት ልማት ድርጅት**
**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

## ድጋሚ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት አቶ መስፍን ስራብዙ እና በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ የሺሀረግ አባቡ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 177759 በ02/07/2014 ዓ.ም በ19/8/2015 ዓ.ም እና በመ/ቁ 134300 በ30/5/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤ.ቁ አዲስ የቦታው ልዩ ስም ጨለለቅ መንደር 7 ተብሎ የሚጠራ ቤት የይዞታ ስፋት በልኬት 255 ካ/ሜ ነው ስፔሻል ፓርክነት የተከለከለ ነው ግሪን ኤሪያነት ያገለግላል ስፔሻል ፓርክ ስለሆነ ስም ዝውውር ማድረግ አይቻልም ሰነድ አልባ ነው የይዞታው በ1997 ዓ.ም አየር ካርታ ላይ ስለማይታይ መብት መፍጠር አይቻልም የሆነው መጫረት የሚፈልግ በፌ/ፍ/አፈ/ዳይሬክቶሬት በሚል C.P.O በብር 1/4ኛ 177,000 በማሲያዝ መሳተፍ የሚችል ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ጥር 7 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡አሁን የሚሸጠው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 428/1/ መሠረት ነው የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፓርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጎብኘት የሚችሉ ሲሆን፤እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ C.P.O የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም C.P.O አሰርተው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ አሰርቶ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመፃፍ ባለፈ ስም የማዘወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ**
**አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**